# ምዕራፍ፡፲፱፡ኦሺያኒያ።

## ታስማኒያ፤ደቡብ፡አውስትራልያ፤ኒውዚላንድ።

፩፤ ታስማኒያ፡ጥንት፡ቫን፡ዲይማንስላንድ፡የተባለውን፡ደሴት፡በሺ፡፲፮፻፵፪፡ታስማን፡የተባለ፡መርከበኛ፡አገኘው። ቀጥሎም፡ካፒቴን፡ኩክ፡የተባለ፡መረመረው። ከታላቅ፡ብሪቴንና፡ከኑሳውት፡ዌልስ፡በደለኞችን፡ወደዚያ፡እየመሰዱ፡ለማኖር፡የተለየ፡ስፍራ፡አደረጉት። ይኸውም፡ቅኝ፡በሺ፡፲፯፻፸፫፡ጀምሮ፡እስከ፡ሺ፡፲፯፻፺፫፡ሰው፡ወደዚያ፡መስደድ፡እስቲቀር፡ድረስ፡የቈየ፡ነበር። ይህም፡ደሴት፡የሚገኘው፡ከዲሱ፡ሆላንድ፡ወደ፡ደቡብ፡ሲል፡ነው። ርዝመቱ፡፪፻፡ማይል፡ይሆናል፤ ሕዝቡ፡፪፻፹፡ሺሕ፡ይሆናሉ፤ ያገሩ፡ስፋት፡፳፮ሺ፡፪፻፲፭፡እስኴር፡ማይል፡ይሆናል።

፪፤ በታስማኒያ፡ብዙ፡ጥቅም፡ያለው፡ሜነራል፡የሚገኝበት፡ይመስላል። ዳሩ፡ግን፡ገና፡አልተከናወነም። ወርቅና፡ብር፡ሌላም፡ከመሬት፡ውስጥ፡የሚገኝ፡ነገር፡ሁሉ፡መልቶበታል። ባገሩ፡ውስጥ፡ከሰል፡በብዙ፡ይገኛል። ብረት፡ባገሩ፡ሁሉ፡ሞልቶአል፤ ትሩፍ፡ነው። በሺ፡፲፰፻፸፩፡መጀመሪያ፡የባቡር፡መንገድ፡ተሠራ። ቀጥሎ፡በሺ፡፲፰፻፸፯፡ለንግድ፡ተብሎ፡፪፻፸፭፡ማይል፡የሚሆን፡ርዝመት፡ያለው፡የባቡር፡መንገድ፡ተሠራ። ታስማኒያ፡የመንግሥት፡ገንዘብ፡የሆነ፡ቴሌግራፍ፡አለው። የተሠራውም፡በቅኚው፡አገር፡ውስጥ፡በሚኖሩት፡ሕዝብ፡ነው።

፫፤ የአውስትራልያ፡ደቡብ፡ክፍል፡መጀመርያ፡የፊሊጵ፡ፖርት፡አውራጃ፡ይባል፡ነበር። ምክንያቱም፡መልካም፡የመርከብ፡መቆሚያ፡ስለ፡ተገኘበት፡ነው። አሁን፡ቢክቶሪያ፡አውራጃ፡በተባለው፡ተእንግሊዝ፡አገር፡እየመጡ፡ብዙ፡ሕዝብ፡ይኖሩበታል። በሺ፡፲፰፻፶፩፡የተገኘውን፡ወርቅ፡ከተራራው፡ውስጥ፡ሥር፡ለመቆፈር፡ተሌላው፡ዓለም፡ክፍል፡የመጡት፡በዚያው፡ይገኛሉ።

፬፤ ደቡብ፡አውስትራልያ፡በመኻከለኛ፡ሰሜን፡ከአውስትራልያ፤በደቡብ፡ከውቅያኖስ፡ይዋሰናል። መሬቱ፡እንደ፡ነገሩ፡ለም፡ነው። ለበጎች፡መሠማርያ፡ይሆናል። ነገር፡ግን፡አገሩን፡ድርቅ፡ያጠቃዋል። ከአውስትራልያ፡የተለየ፡ነው። አየሩ፡ጥሩ፡ጤናማ፡ነው። በበጋ፡ጊዜ፡እጅግ፡ሙቀት፡ነው፡በሌላ፡ጊዜ፡ግን፡አየሩ፡መጠነኛ፡ነው።

፭፤ ባገሩ፡ውስጥ፡ከመሬት፡ውስጥ፡እየተቆፈረ፡ለሚወጣው፡ነገር፡በብዙ፡ይሠራል። ብዙ፡የሚኒራል፡ሀብት፡ይገኛል። በዚሁም፡አብልጦ፡ነሐስ፡ይገኛል። ሙንታ፤ዋልሩ፤ቡራ፡በጣም፡ሰፊ፡ጉድጓዶች፡(ማይንስ፡)ስለ፡ሆኑ፡፫ሺ፡ሠራተኞች፡አሉባቸው። የደቡብ፡አውስትራልያ፡ሰፊ፡የቴሌግራፍ፡ሽቦ፡አለበት። ፬ሺ፡፩፻፶፱፡ማይል፡የሚሆን፡ፌት፡ተሠርቷል። አንዱ፡ሽቦ፡በአውስትራልያ፡መኻከል፡አድርጎ፡ወደ፡ፖርት፡ደርዊን፤በሰሜን

ጠረፍ ፡ ፪ሺ ፡ ማይል ፡ ወደ ፡ እንግሊዝ ፡ ሰብመሪን ፡ ሽቦ ፡ ይገጥማል ። እንዲሁ አድርጎ ፡ በአውስትራልያ ፡ ያለው ፡ የቴሌግራፍ ፡ መገናኛ ፡ ተዓለም ፡ ክፍል ፡ ሁሉ ጋር ፡ ይገናኛል ።

፯ ፤ የኙዚላንድ ፡ ቅኝ ፡ አገር ፡ ባንድነት ፡ የተሰበሰበ ፡ ሦስት ፡ ደሴቶች ፡ አሉበት ። እነርሱም ፡ የሰሜን ፡ መኻከለኛ ፡ የእስቱዋርት ፡ ደሴት ፡ ተብለው ፡ የታወቁ ናቸው ። አንደኛውን ፤ ምንም ፡ ሰው ፡ አልያዘውም ። እነዚህ ፡ ሁሉም ፡ ፩ሺ ማይል ፡ ርዝመት ፡ ፪፻ ፡ ማይል ፡ ስፋት ፡ አላቸው ። በጠረፋቸው ፡ ከሺ ፡ የሚበዙ ፡ ማረፊያዎች ፡ አሉዋቸው ። ያገሩ ፡ ስፋት ፡ ፷፰ ፡ ሚሊዮን ፡ ኤክር ፡ ይገመታል ።

፰ ፤ ኙዚላንድን ፡ ቀድሞ ፡ በሺ ፡ ፯፻፷፱ ፡ ካፒቴን ፡ ኩክ ፡ የተባለ ፡ ሰው ፡ አገኘው ። በጣም ፡ ደስ ፡ የሚያሰኘውን ፡ የካፒቴን ፡ ኩክን ፡ ታሪክ ፡ እንዴት ፡ አድርጎ ፡ በባሕር ፡ ላይ ፡ እንደ ፡ ተጓዘና ፡ ዓለምን ፡ እንደ ፡ ዞረ ፤ ጕበዛዝት ፡ የሆኑ ፡ አላነበቡ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በፍጥነት ፡ እንዲመለከቱ ፡ አጥብቄ ፡ እመክራቸዋለሁ ። ታሪኩን ሲመለከቱ ፡ ብዙ ፡ ልዩ ፡ የሆነ ፡ ድፍረት ፡ ያለበትን ፡ ታሪክ ፡ ያነባሉ ። እርሱ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ስፍሮችን ፡ ተጕበኘ ፡ ወዲህ ፡ ዕውቀትን ፡ ከፍ ፡ ለማድረግ ፡ የተሻለ ፡ አሳብ ፡ ሆነ ።

፱ ፤ የዚሁ ፡ አገር ፡ ሕዝብ ፡ ቍጥር ፡ በፍጥነት ፡ እያነሰ ፡ ሄደ ። ይህም ፡ የሆነው ፡ ወርቅ ፡ ከምድር ፡ ውስጥ ፡ ለማግኘት ፡ ምሬት ፡ የመቆፈር ፡ ብልሀት ፡ ከተገኘ ወዲህ ፡ ነው ። በኙዚላንድ ፡ ብዙ ፡ ሚኒራል ፡ ያለመጠን ፡ እንደሚገኝ ፡ የታመነ ነው ። ጠጕር ፤ በቆሎ ፡ ዱቄት ፤ እነዚህ ፡ ከኙዚላንድ ፡ ወደ ፡ እንግላንድ ፡ የሚሄዱ ፡ ወጪ ፡ ጥና ፡ የንግድ ፡ ዕቃዎች ፡ ናቸው ። በሺ ፡ ፰፻፷፫ ፡ በባላገሮቹና ፡ በእንግዶቹ ፡ መኻከል ፡ ጦርነት ፡ ሆነ ። እንደ ፡ ገና ፡ ደግሞ ፡ በሺ ፡ ፰፻፷፰ ፡ እንዲሁ ፡ ሆነ ።

## ጥያቄ ።

፩ ፤ ታስማኒያ ፡ የቀድሞ ፡ ሰው ፡ ማነው ፡ ?
ያገኘው ፡ ሰው ፡ ማን ፡ ይባላል ፡ ?
መርማሪው ፡ ማነው ፡ ?
የሕዝብ ፡ ብዛት ፡ እንዴት ፡ ነው ፡ ?

፪ ፤ ማዕድንሳ ፡ እንዴት ፡ ነው ፡ ?
ከሰል ፡ ወዴት ፡ ይገኛል ፡ ?
ታላቅ ፡ የከሰል ፡ ጕድጓድ ፡ የት ፡ ነው ፡ ?
ስፋቱ ፡ የቱን ፡ ያህላል ፡ ? ብረትሳ ፡ ?

፫ ፤ ወርቅ ፡ የሚቆፍሩት ፡ ወዴት ፡ ይሄዳሉ ፡ ?
የቀድሞ ፡ ስሙ ፡ ማነው ፡ ?

፬ ፤ የደቡብ ፡ አውስትራልያ ፡ እንዴት ፡ ይዋሰናል ፡ ?

መሬቱ ፡ እንዴት ፡ ያለ ፡ ነው ፡ ? አየሩሳ ፡ ?

፫ ፤ የማዕድን ፡ ሀብት ፡ እንዴት ፡ ነው ፡ ?

ቴሌግራፍ ፡ እንዴት ፡ ነው ፡ ?

፬ ፤ በኙዚላንድ ፡ ምን ፡ ይገኛል ፡ ?

ስፋቱ ፡ ምን ፡ ያህላል ፡ ?

፭ ፤ መጀመርያ ፡ ማን ፡ ጐበኘው ፡ ?

፮ ፤ የሕዝቡ ፡ ብዛትና ፡ ማዕድኑም ፡ እንዴት ፡ ነው ፡ ?

ስለ ፡ ጦርነት ፡ እንዴት ፡ ነው ፡ ?

## ምዕራፍ ፡ ፱፻፬ ።

### ፖሊኒሲያ ፡ የባንድዊች ፡ ደሴቶች ።

፩ ፤ የሦስተኛው ፡ ውቅያኖስ ፡ ክፍል ፡ ፖሊኒሲያ ፡ ይባላል ። በዚህም ፡ አያሎች ፡ በፓስፊክ ፡ ውቅያኖስ ፡ የተበተኑ ፡ ትንንሾች ፡ ደሴቶች ፡ አሉበት ። በነዚህ ፡ ደሴቶች ፡ ውስጥ ፡ ከሠለጠኑት ፡ ሕዝብ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ አይገኝም ፡ (ፈረንጆች ፡ አልገቡበትም ። )

፪ ፤ በሺ ፡ ፯፻፸፰ ፡ ካፒቴን ፡ ኩክ ፡ ያገኛቸው ፡ ሳንድ ፡ ዊች ፡ የተባሉት ፡ ደሴቶች ፡ በፖሊኒሲያ ፡ ዋና ፡ አገሮች ፡ ናቸው ። በምሥራቅ ፡ ፳ሺ ፡ ማይል ፡ የሚያህል ፡ ርዝመት ፡ ወደ ፡ ቻን ፡ አገር ፡ ተዘርግተዋል ። ደግሞ ፡ ፪ሺ፫፻ ፡ ወደ ፡ ሜክሲኮ ፡ ምዕራብ ፡ ተበትነዋል ። ሀዋይ ፡ ወይም ፡ አዋዬ ፡ የተባለው ፡ ደሴት ፡ ከሁሉም ፡ ይሰፋል ። የዌልስን ፡ ግማሽ ፡ ያህላል ። በቮልካኖው ፡ ስመ ፡ ጥሩ ፡ ነው ። ከነዚህ ፡ አንዱ ፡ ሞና ፡ ሎዋ ፡ የተባለው ፡ ፲፫ሺ ፡ ፯፻፶ ፡ ፊት ፡ ከፍታ ፡ አለው ። አየሩም ፡ ጤናማ ፡ መሬቱም ፡ ፍሬያም ፡ ነው ።

፫ ፤ ካፒቴን ፡ ኩክ ፡ በዚሁ ፡ አገር ፡ መልካቸው ፡ እጅግ ፡ ያማረ ፡ ውቦች ፡ የሆኑትን ፡ ሕዝብ ፡ አገኘ ። መልካቸው ፡ ከኛ ፡ ይልቅ ፡ ይጠቍራል ። ደስታ ፡ የመላቸው ፡ የሰው ፡ ፍቅር ፡ ያላቸው ፡ ሕዝብ ፡ ይመስላሉ ። እነርሱም ፡ ኩክን ፡ እንደ ፡ አንድ ፡ አምላክ ፡ ቈጠሩት ።

፬ ፤ ነገር ፡ ግን ፡ በመኻከላቸው ፡ አንድ ፡ የሚያስደነግጥ ፡ ልማድ ፡ ነበራቸው ። ይህም ፡ የሰው ፡ ሥጋ ፡ እየበሉ ፡ በዓል ፡ አድርገው ፡ መፈንጠዛቸውና ፤ ሰውን ፡ ለጣዖታቸው ፡ መሥዋዕት ፡ ማቅረባቸው ፡ ነው ። ደግሞም ፡ ሌብነታቸው ፡ አያድርስ ፡ ነው ። ሌላም ፡ ብዙ ፡ ክፋት ፡ አላቸው ።

፭ ፤ ባላገሮቹ ፡ በመጀመርያ ፡ ካፒቴን ፡ ኩክን ፡ በጣም ፡ የወዳጅነት ፡ አኳኋን አሳዩት ። ከጥቂት ፡ ጊዜ ፡ በኋላ ፡ ከመርከቦቹ ፡ አንዱን ፡ ሰረቁት ፡ ካፒቴንም ፡ የተሰረቀውን ፡ እስቲያገኝ ፡ ድረስ ፡ የሀዋይን ፡ ንጉሥ ፡ ለማሰር ፡ ወደ ፡ ጠረፍ ፡ ሄደ ።

፮ ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ወደ ፡ ጠረፉ ፡ ሲደርስ ፡ ባላገሮቹ ፡ ብዙ ፡ ሆነው ፡ ተሰልፈው ፡ ስለ ፡ ቈዩት ፡ የካፒቴን ፡ ኩክ ፡ ሰዎች ፡ መርከብ ፡ ይዘው ፡ ይጠብቁት ፡ ነበርና ፡ ወደ ሰዎቹ ፡ መመለስ ፡ አስፈለገው ። ባላገሮቹም ፡ መሣርያቸውን ፡ እያወዛወዙ ፡ ደንፊያም ፡ እየወረወሩበት ፡ እየተጩዋጩዋሁ ፡ ተከታተሉት ።

፯ ፤ ካፒቴን ፡ ኩክ ፡ ጠመንጃውን ፡ እንጣጠረባቸው ፤ እጅግም ፡ አድርጎ ፡ እንዲፈሩህ ፡ ብቻ ፡ አደረገ ። ቀጥሎ ፡ አነጣጠረና ፡ አንዱን ፡ እፊት ፡ ቀድሞ ፡ የተገኘውን ፡ ባላገር ፡ ተኩሶ ፡ ጣለው ። ገና ፡ የተኩሱ ፡ ጢስ ፡ ሳይጠፋ ፡ ባላገሮቹ ፡ ገሥገሡና ፡ በዱላ ፡ ተረከኩት ። ቀጥለው ፡ በጩቤ ፡ ሻጡበት ፤ የርሱም ፡ ሰዎች ፡ ጠመንጃ ፡ ተኰሱባቸው ። ዳሩ ፡ ግን ፡ እርሱን ፡ አላዳኑትም ።

፰ ፤ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ የሳንድ ፡ ዊችን ፡ ደሴቶች ፡ ታላላቅ ፡ መርከቦች ፡ ይጐበኙዋ ቸው ፡ ጀመር ። በዚያ ፡ የሚያልፍ ፡ መርከብ ፡ የተባለ ፡ ሁሉ ፡ እነርሱን ፡ የማይ ጐበኝ ፡ የለም ። ኦኖኖሉ ፡ የተባለው ፡ አንድ ፡ ትንሽ ፡ ደሴት ፡ በካሊፎርኒያ ፡ በች ኀና ፡ በአውስትራልያ ፡ መኻከል ፡ ለሆነው ፡ ንግድ ፡ ዋና ፡ የንግድ ፡ ስፍራ ፡ ሆነ ። በዚያ ፡ ከሚኖሩት ፡ ባላገሮች ፡ ግን ፡ ከነርሱ ፡ አንዳች ፡ ጠቀሜታ ፡ አይገኝባቸውም ።

፱ ከቀድሞ ፡ ይልቅ ፡ ክፋት ፡ እየጨመሩ ፡ ሄዱ ። ብዙ ፡ በሽታ ፡ ስለ ፡ አላቸው ፡ ሕዝቡ ፡ ከቍጥር ፡ ይጐድላሉ ። ካራት ፡ ሺሕ ፡ ሰው ፡ መቶ ፡ አምሳ ፡ ብቻ ፡ ቀሩ ። ደሴቱ ፡ ያለ ፡ ሰው ፡ ባዶውን ፡ እንዳይቀር ፡ ያስፈራል ።

፲ ፤ ተእንግሊዞችና ፡ ተአሜሪከች ፡ ጥቂቶች ፡ የወንጌል ፡ መምህራን ፡ በነዚህ ፡ ደሴቶች ፡ የሚኖሩትን ፡ ምስኪኖች ፡ ከጥፋት ፡ ለማዳን ፡ ወደዚያ ፡ ተሻግረው ፡ ነበርና ፡ ወንጌልን ፡ ሰበኩላቸው ፡ የትምህርት ፡ ቤትም ፡ አቆሙላቸው ። በዚህም ፡ ያገሩ ፡ ልጆች ፡ ቅዱስ ፡ መጽሐፍን ፡ ለማንበብ ፡ ቻሉ ።

፲፩ ፤ ካሹማና ፡ የሳንድ ፡ ዊች ፡ ደሴቶች ፡ ንግሥት ፡ እንደራሲ ፡ የክርስቲያንን ፡ ሃይ ማኖት ፡ ስለ ፡ ተቀበለች ፡ በርስዋ ፡ ርዳታ ፡ የሚሲዮኖች ፡ ሥራቸው ፡ ተከናወ ነላቸውና ፡ አያል ፡ የትምህርት ፡ ቤቶች ፡ ተመሠረቱ ።

፲፪ ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ካሹማና ፡ ስለ ፡ ሞተች ፡ የርስዋ ፡ ሞት ፡ ለሳንድ ፡ ዊች ፡ ደሴ ቶች ፡ ትልቅ ፡ አለመታደል ፡ ሆነ ። ከባላገሮቹ ፡ አያሎች ፡ ከክፋታቸው ፡ ተመ ለሱ ። ነገር ፡ ግን ፡ እስከ ፡ አሁን ፡ ሚሲዮኖች ፡ በውነት ፡ የበጎነት ፡ ሥራ ፡ ይሠ ሩላቸዋል ። ድካማቸው ፡ ያልተከናወነላቸው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በውነት ፡ በሳንድ ፡ ዊች ፡ ደሴቶች ፡ የሚኖሩ ፡ ባላገሮች ፡ በገዛ ፡ ክፋታቸው ፡ በመጨረሻው ፡ ከምድር ፡ ላይ ፡ እንዲጠፉ ፡ ጥርጥር ፡ የለበትም ።

፲፫ ፤ ላድሮንስ ፡ የተባሉት ፡ ደሴቶች ፡ ቍጥራቸው ፡ ፳ ፡ ይሆናል ። ያሉበትም ፡ ክፌ ልፒን ፡ ደሴት ፡ ምሥራቅ ፡ ነው ። በሺ ፡ ፭፻፳፩ ፡ ያገኛቸው ፡ በእስጳኞች ፡ ሥራ ፡ ውስጥ ፡ የነበረ ፡ ማጋልሀንስ ፡ የተባለ ፡ የፖርቱጋል ፡ መርከበኛ ፡ ነው ። ያገሩ ፡ ሰዎች ፡ ሌቦች ፡ ስለ ፡ ነበሩ ፡ ላድሮንስ ፡ ይላቸው ፡ ነበር ። በእስጳንያ ፡ ቋንቋ ፡ ላድ ሮንስ ፡ ማለት ፡ ቀሳጢ ፡ እንደማለት ፡ ነው ። በኋላ ፡ የእስጳንያ ፡ ንግሥት ፡ ያራ ተኛ ፡ ፊሊጵን ፡ ሚስት ፡ ስለ ፡ ማክበር ፡ ማርያን ፡ ደሴቶች ፡ ተባሉ ።

፲፬ ፤ ፪፳ ፡ ማይል ፡ ወደ ፡ ደቡብ ፡ ራቅ ፡ ብለው ፡ በጃንና ፡ በአውስትራልያ ፡ መኻከል ፡ ያሉት ፡ ደሴቶች ፡ ክሮሊና ፡ ይባላሉ ። እነዚህም ፡ አያሎች ፡ ናቸው ። ከምሥራቅ ፡ እስከ ፡ ምዕራብ ፡ ያለው ፡ ርቀታቸው ፡ ፪ሺ ፡ ፳፻ ፡ ማይል ፡ ይሆናል ። በእስጳንያው ፡ በ፪ኛው ፡ ቻርልስ ፡ ስም ፡ ይጠራሉ ።

፲፭ ፤ በዚህ ፡ ደሴት ፡ ሸንኮር ፡ አገዳ ፡ ሙዝ ፡ ሌላም ፡ የሚበላ ፡ ቅጠላቅጠልና ፡ ፍሬ ፡ ሁሉ ፡ ይገኛል ። የፖሊኒሲያ ፡ ባላገሮች ፡ ከሁሉ ፡ ይልቅ ፡ የኮኮዋን ፡ ዛፍ ፡ በጣም ፡ ያከብራሉ ። ምክንያቱም ፡ በሥሩ ፡ ተቀምጠው ፡ የሚያርፉበት ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ነው ። ፍሬውንም ፡ ለምግብ ፡ ያደርጉታል ።

፲፮ ፡ የነት ፡ ፍሬ ፡ እንደ ፡ ቅል ፡ ለጥቅም ፡ ይሆናል ። ቅጠሉንም ፡ መሶብ ፡ ወይም ፡ ቅርጫት ፡ ያበጁታል ። ግንዱም ፡ ለማገዶ ፡ ይሆናል ። ልጡም ፡ እየ ጨረተ ፡ ለዓሣ ፡ መያዣ ፡ ሲባጎ ፡ ይሆናል ። ገመድ ፡ ይሠሩታል ። ክንፉን ፡ እየቈረጡ ፡ ለቤት ፡ ይከድኑታል ። በዘንጉም ፡ ጀልባ ፡ ይቀዝፉበታል ። የርሱ፡ ዕንጨት ፡ ለብዙ ፡ ጥቅም ፡ ይሆናቸዋል ።

## ጥ ያ ቄ ።

፩ ፡ ፖሊሲኒያ ፡ እንዴት ፡ ያለ ፡ ነው ፡ ? ባላገሮቹ ፡ ምንድን ፡ ናቸው ፡ ?

፪ ፡ ከሁሉም ፡ ዋናው ፡ ደሴት ፡ የትኛው ፡ ነው ፡ ?

በ፲፯፻፸፰ ፡ እነዚህን ፡ ደሴቶች ፡ ያገኛቸው ፡ ማነው ፡ ?

ሳንድ ፡ ዊች ፡ ከተባሉት ፡ ደሴቶች ፡ ታላቁ ፡ የትኛው ፡ ነው ፡ ?

ኦሂ ፡ የተባለው ፡ ደሴት ፡ ስመ ፡ ጥሩነቱ ፡ በምንድነው ፡ ?

ሞና ፡ ሎዋ ፡ በተባለው፡ደሴት፡በልካኖ፡የፈነዳው፡ምን፡ጊዜ ፡ ነው ፡ ?

፫ ፡ በሳንድ ፡ ዊች ፡ ደሴት ፡ ካፒቴን ፡ ኩክ፡ያገኛቸው ፡ ባላገሮች፡እንዴት ፡ ያሉ ፡ ናቸው ፡ ?

፬ ፡ የእኩሊቶቹ ፡ ልማዳቸው ፡ እንዴት ፡ ነው ፡ ?

፭ ፡ በባላገሮቹና ፡ በካፒቴን ፡ ኩክ ፡ መኻከል ፡ ምን ፡ ነገር ፡ ተነሣ ፡ ?

፮ ፡ ካፒቴን ፡ ኩክ ፡ አስፈላጊ ፡ ነገር ፡ ሆኖ ፡ ያገኙው ፡ ምንድነው ፡ ? የሆነውን ፡ ተናገር ፡ ተርክ ።

፯ ፡ ወደ ፡ ሳንድ ፡ ዊች ፡ ደሴት ፡ ለመርዳት ፡ብለው ፡ በፍጥነት ፡ የመጡት ፡ የማን ፡ መርከቦች ፡ ናቸው ፡ ?

ነጮች ፡ ከባላገሮች ፡ ጋር ፡ በመተዋወቅ ፡ ምን ፡ ጥቅም ፡ አገኙበት ፡?

፲ ፡ የእንግሊዝና ፡ የአሚሪካ ፡ ሚሲዮኖች ፡ ምን ፡ አደረጉ ፡ ?

፲፩ ፡ ካሁማና ፡ እንዴት ፡ ሆነች ፡ ?

፲፪ ፡ የሞቷ ፡ ስበብ ፡ ምንድን ፡ ነበር ፡ ? ሚሲዮኖች ፡ እንዴት ፡ ሆኑ ?

፲፫ ፡ ላድሮንስ ፡ የተባሉት ፡ ደሴቶች ፡ እንዴት፡ናቸው ፡ ? እንደምን፡ተገኙ፡? እንዲህ ፡ ያለ ፡ ስም ለምን ፡ ወጣላቸው ፡ ? በኋላ ፡ ማን ፡ ተብለው ፡ ተሠየሙ ፡ ?

፲፬ ፡ ካሮሊና ፡ የተባሉት ፡ ደሴቶች ፡ እንደምን ፡ ሆኑ ፡ ? ስፋታቸው ፡ እንዴት ፡ ነው ፡ ?

፲፭ ፡ ምን ፡ ፍሬ ፡ ይሰጣሉ ፡ ?

፲፮ ፡ በሥራ ፡ ረገድ ፡ እንዴት ፡ ናቸው ፡ ?

## ምዕራፍ ፡ ፩፻፫ ።

### ፖሊኔሲያና ፡ የተሰበ ሰቡ ፡ ደሴቶች ።

፩ ፤ ሶሳይቲ ፡ አይላንድስ ፡ የተባሉ ፡ ደሴቶች ፡ እንደዚሁ ፡ ቊጥራቸው ፡ ወደ ፡ ፖሊኔሲያ ፡ ነው ። ያሉበትም ፡ ተኤክዋቶር ፡ ደቡብ ፡ ሺ፫፻ ፡ ማይል ፡ በሚሆን ፡ ርቀት ፡ ነው ። ሳንድዊች ፡ ደሲቶች ፡ ካሉበት ፡ ከሰሜን ፡ ወገን ፡ ይርቃል ።

፪ ፤ ከሶሳይቲ ፡ አይላንድስ ፡ የሚበልጠው ፡ ደሴት ፡ ታሂቲ ፡ ወይም ፡ አታሂቲ ፡ ይባላል ። ዙሪያው ፡ ፻፳ ፡ ማይል ፡ ይሆናል ። ከፍ ፡ ባለው ፡ ተራራው ፡ ሁኖ ፡ ገጹ ፡ በሕር ፡ ይታያል ። የሚኖሩበትም ፡ ሕዝብ ፡ ቊጥራቸው ፡ ዐሥር ፡ ሺሕ ፡ ይሆናሉ ። መጀመርያ ፡ ወደ ፡ ፖሊኔሲያ ፡ የሄዱት ፡ ሚሲዮኖች ፡ ወደ ፡ አታሂቲ ፡ ተላኩ ። ባላገሮቹ ፡ መልካቸው ፡ የአማሩና ፡ ለማየት ፡ ደስ ፡ የሚያሰኙ ፡ ናቸው ።

፫ ፤ ከብዙ ፡ ዓመታት ፡ አስቀድሞ ፡ በነዚህ ፡ ደሴቶች ፡ መኻከል ፡ አንድ ፡ የሚያስገርም ፡ ነገር ፡ ሆኖአል ። የእንግሊዝ ፡ መርከበኞች ፡ ገንዘብ ፡ የነበረች ፡ አንዲት ፡ ብሪግ ፡ በውንቲ ፡ የተባለች ፡ መርከብ ፡ ምግብና ፡ ፍሬ ፡ ከሶሳይቲ ፡ አይላንድስ ፡ ወደ ፡ ዌስት ፡ ኢንዲስ ፡ ለመውሰድ ፡ ተልካ ፡ ነበር ። የዚችው ፡ መርከብ ፡ ዋና ፡ ሹም ፡ ሌፍትናንት ፡ ዊልያም ፡ ብላይት ፡ ይባላል ።

፬ ፤ በሺ ፡ ፯፻፹፰ ፡ በአታሂቲ ፡ ደረሰ ። መርከበኞቹ ፡ ደሴቱን ፡ አዩና ፡ ደስ ፡ አላቸው ። አየሩ ፡ ጥሩና ፡ ብሩህ ፡ ነው ። እያንዳንዱ ፡ ዛፍ ፡ ፍሬ ፡ አንጀርጓል ። በዚያ ፡ ለእንጀራ ፡ ተብሎ ፡ ከመሬት ፡ ጋር ፡ ብዙ ፡ መጣር ፡ የለም ። ዛፎች ፡ አብስለው ፡ ለምግብ ፡ አድርሰዋልና ፤ ፍጹም ፡ ፍሬው ፡ እንደ ፡ ተጋገረ ፡ ምግብ ፡ ሆኖአል ።

፭ ፤ የአታሂቲ ፡ ባላገሮች ፡ እንግሊዞችን ፡ በቸርነት ፡ ይቀበሉዋቸዋል ። ሴቶቹም ፡ ማዕበል ፡ ያንገላታቸውን ፡ መርከበኞች ፡ በታላቅ ፡ ፍቅር ፡ ይራሩላቸዋል ። በጭሩ ፡ መርከበኞች ፡ ጊዜያቸውን ፡ በመልካም ፡ ያሳልፉት ፡ ነበር ።

፮ ፤ በባሕር ፡ ከመዞር ፡ ይልቅ ፡ መኖሪያቸው ፡ በዚህ ፡ ደሴት ፡ እንዲሆን ፡ ተመኝተው ፡ ነበር ። መርከቢቱ ፡ በውንቲ ፡ ከዚያ ፡ በተነሣች ፡ ጊዜ ፡ ያማረውን ፡ ጠረፍ ፡ በመተዋቸው ፡ በጣም ፡ ያዝኑ ፡ ነበር ። የሚመለሱበትን ፡ ቀን ፡ አልወሰኑም ፡ ነበርና ፡ ብዙ ፡ ቀን ፡ አልሄዱም ።

፯ ፤ ለዚች ፡ መርከብ ፡ ዋና ፡ ሹም ፡ የነበረው ፡ አንድ ፡ ክርስቲያን ፡ የተባለ ፡ ኰልማሳ ፡ ነበር ። ከሌፍትናንት ፡ ብላይት ፡ ጋራ ፡ ስምምነት ፡ አልነበረውምና ፡ መርከበኞቹን ፡ ባለቃቸው ፡ ላይ ፡ አስነሥቶ ፡ መርከቡን ፡ ወስዶ ፡ ለመሸፈት ፡ አስዶለተ ።

፰ ፤ አንድ ፡ ቀን ፡ ማለዳ ፡ ገና ፡ ፀሐይ ፡ ስትወጣ ፡ ክርስቲያን ፡ ከነሰዎቹ ፡ ካፒቴን ፡ ብላይት ፡ ተኝቶ ፡ ሳለ ፡ ወደ ፡ መኝታው ፡ ጓዳ ፡ ገቡ ። እጆቹን ፡ ወደ ፡ ኋላው ፡ አሠሩና ፡ ወዲያና ፡ ወዲህ ፡ በማለት ፡ ለማምለጥ ፡ የፈተንህ ፡ እንደ

ሆን ፡ እንገድልሃለን ፡ ብለው ፡ አስፈራሩት ። ወደ ፡ አንዲት ፡ ቀዳዳ ፡ ታንኳ ፡ አግ
ብተው ፡ ተውት ። ክርሱም ፡ ጋር ፡ ለዚህ ፡ ሽፍትነት ፡ አንተባበርም ፡ ብለው ፡
የሞገዱ ፡ ሌሎች ፡ ፲፰ ፡ ሰዎች ፡ አብረውት ፡ ነበሩ ።

፱ ፡ በብዙ ፡ መከራና ፡ ጭንቅ ፡ ሌፍትናንት ፡ ብላይትና ፡ ጓደኞቹ ፡ በደኅና ፡ ወደ ፡ እንግላንድ ፡ ደረሱ ። ፖንዶራ ፡ የተባለችው ፡ የእንግሊዝ ፡ የጦር ፡ መርከብ ፡ የሸፈቱትን ፡ ለመፈለግና ፡ ሽፍቶቹ ፡ ተይዘው ፡ መጥተው ፡ ወደ ፡ ፍርድ ፡ እንዲቀርቡ ፡ ለማድረግ ፡ ታዘዘች ።

፲ ፡ የጦር ፡ መርከቢቱም ፡ ወደ ፡ አታሂቲ ፡ በደረሰች ፡ ጊዜ ፡ ከሽፍቶቹ ፡ ፲፬ቱን ፡ አግኝታ ፡ ወደ ፡ እንግላንድ ፡ አመጣቻቸውና ፡ ሦስቱ ፡ በፍርድ ፡ ተሰቀሉ ።

፲፩ ፡ የሽፍቶቹ ፡ መሪ ፡ ክርስቲያን ፡ አያሎች ፡ ጓደኞቹን ፡ ይዞ ፡ ባውንቲ ፡ በተባለችው ፡ መርከብ ፡ አስቀድሞ ፡ ከአታሂቲ ፡ ከደሴቱ ፡ አፈትልኮ ፡ ሸሽቶ ፡ ነበረና ፡ አልተገኘም ፡ አልተያዘም ። እነዚህም ፡ በሄዱ ፡ ጊዜ ፡ ብዙ ፡ አሳሞች ፡ ውሾች ፡ ድመቶች ፡ ዶሮችም ፡ ደግሞ ፡ ከደሴቱ ፡ ከአታሂቲ ፡ የነበሩትን ፡ ሴቶችና ፡ ወንዶች ፡ ሁሉ ፡ ይዘው ፡ ሄደዋል ።

፲፪ ፡ ክርስቲያንና ፡ ጓደኞቹ ፡ እነዚህን ፡ ሁሉ ፡ ይዘው ፡ ከጠፉ ፡ በኋላ ፡ ከቶ ፡ በዚህ ፡ ስፍራ ፡ ደረሱ ፡ በእንደዚህ ፡ ያለ ፡ ቦታ ፡ ታዩ ፡ ሳይባል ፡ ብዙ ፡ ዘመን ፡ አለፈ ። የደረሱበትን ፡ ስፍራ ፡ የሚያውቅ ፡ አንድም ፡ ሰው ፡ አልተገኘም ። የሄዱባትም ፡ መርከብ ፡ ባውንቲ ፡ የደረሰችበት ፡ ታጣ ፡ ምንም ፡ ወሬ ፡ አልተገኘም ። መላው ፡ ዓለም ፡ ግን ፡ መርከቢቱ ፡ ከነሰዎቹዋ ፡ ወደ ፡ ውቅያኖስ ፡ ባሕር ፡ ሰጥማለች ፡ ብሎ ፡ አመነ ።

## <u>ጥያቄ ።</u>

፩ ፡ ሶሳይቲ ፡ አይላንድስ ፡ የተባሉ ፡ ደሴቶች ፡ በየት ፡ በኩል ፡ ናቸው ፡ ?
የየትኞች ፡ ደሴቶች ፡ ክፍል ፡ ናቸው ፡ ?

፪ ፡ የአታሂቲ ፡ ደሴት ፡ ስፋትና ፡ የሕዝቡ ፡ ብዛት ፡ እንዴት ፡ ነው ፡ ?
ባላገሮቹ ፡ እንዴት ፡ ያሉ ፡ ናቸው ፡ ?

፫ ፡ ብሬግ ፡ ባውንቲ ፡ የተባለችው ፡ መርከብ ፡ እንዴት ፡ ሆነች ፡ ?
የመርከቢቱ ፡ ዋና ፡ አዛዥ ፡ ማን ፡ ይባል ፡ ነበር ፡ ?

፬ ፡ በአታሂቲ ፡ ምን ፡ ጊዜ ፡ ደረሰች ፡ ?
ሰዎቹ ፡ ደሴቱን ፡ የቱን ፡ ያህል ፡ ወደዱት ፡ ?

፭ ፡ ባላገሮቹ ፡ እንግሊዞችን ፡ እንደ ፡ ምን ፡ አድርገው ፡ ተቀበሉዋቸው ፡ ?

፮ ፡ መርከቢቱን ፡ ባውንቲን ፡ ይዘው ፡ የጠፉ ፡ መርከበኞች ፡ እንደ ፡ ምን ፡ ሆኑ ፡ ?
ምን ፡ ቍርጥ ፡ አሳብ ፡ አደረጉ ፡ ?

፯ ፡ ክርስቲያን ፡ የተባለው ፡ ሰውዬ ፡ ምን ፡ አደረገ ፡ ?

፰ ፡ ሌፍትናንት ፡ ብላይትንና ፡ ሌሎቹንም ፡ ፲፰ ፡ ሰዎች ፡ ምን ፡ አደረጋቸው ፡ ?

፱ ፡ ወደ ፡ እንግላንድ ፡ ደረሱን ፡ ?
ወደ ፡ አታሂቲ ፡ እንዴት ፡ ያለ ፡ መርከብ ፡ ተላከ ፡ ?
፲ ፡ ፖንዶራ ፡ እንደ ፡ ምን ፡ ሆነ ፡ ? ሽፍቶቹ ፡ እንደምን ፡ ሆኑ ፡ ?
፲፩ ፡ ክርስቲያንና ፡ ጓደኞቹ ፡ እንዴት ፡ አደረጉ ፡ ?
፲፪ ፡ ምን ፡ የሆኑ ፡ ይመስላል ፡ ?

## ምዕራፍ ፡ ፻፲፰ ፡ ኦሺያኒያ ።

### የመርከቢቱ ፡ የባውንቲ ፡ ታሪክ ፡ መጨረሻ ።

፩ ፡ ስለ ፡ ባውንቲ ፡ መርከብ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ንግግር ፡ ከተወ ፡ ፳ ፡ ዘመን ፡ ካለፈ ፡ በኋላ ፡ መርከቢቱ ፡ ባውንቲ ፡ እንዴት ፡ እንደ ፡ ሆነች ፡ ትንሽ ፡ ወሬ ፡ ብቅ ፡ አለ ። በሺ ፡ ፰፻፰ ፡ በደቡብ ፡ አሜሪካ ፡ የእንግሊዝ ፡ የጦር ፡ መርከብ ፡ ማርከዊ ፡ ከተባለ ፡ ደሴት ፡ ተነሥቶ ፡ ወደ ፡ ቫልባሬሶ ፡ ያልፍ ፡ ነበር ። የመርከቡ ፡ ዋና ፡ ካፒቴን ፡ ሰር ፡ ቶማስ ፡ እስቴን ፡ ይባላል ።

፪ ፡ በመርከብ ፡ ሲሄድ ፡ የፒትካይርን ፡ ደሴት ፡ አልፎ ፡ መልህቅ ፡ ሰደደ ። ይህ ፡ ትንሽ ፡ ደሴት ፡ ያለው ፡ ከአታሂቲ ፡ በደቡብ ፡ ምሥራቅ ፡ ነው ። ቀድሞ ፡ በሺ ፡ ፯፻፷፯ ፡ ካፒቴን ፡ ካርትርት ፡ አግኝቶት ፡ ነበር ። ምንም ፡ የሚጠቅም ፡ ነገር ፡ የማይገኝበት ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ሰው ፡ የሚኖርበት ፡ አይመስልምና ፡ ከዚያ ፡ ወዲህ ፡ ደሴቱን ፡ የጐበኙት ፡ ሰዎች ፡ ጥቂቶች ፡ ናቸው ።

፫ ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ሰር ፡ ቶማስ ፡ እስቴን ፡ በመርከብ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ወደ ፡ ጠረፍ ፡ ቢመለከት ፡ በደሴቱ ፡ ውስጥ ፡ እርሻና ፡ ትንንሽ ፡ ቤቶች ፡ ቢያይ ፡ እጅግ ፡ ተገረመ ። እነዚህ ፡ ቤቶች ፡ ደግሞ ፡ የአረማውያንን ፡ ቤቶች ፡ አይመስሉም ። ነገር ፡ ግን ፡ አረማውያን ፡ ከሚሠሩዋቸው ፡ ቤቶች ፡ ይልቅ ፡ የተሻሉ ፡ ሁነው ፡ ተሠርተዋል ። በእንግሊዝ ፡ አገር ፡ የሚሠሩትን ፡ የድኆችን ፡ ቤቶች ፡ ይመስላሉ ።

፬ ፡ ሰር ፡ ቶማስ ፡ እስቴንና ፡ መርከበኞቹ ፡ በዚህ ፡ ነገር ፡ ሲገረሙ ፡ ሳሉ ፡ አንዲት ፡ ትንሽ ፡ ታንኳ ፡ ከጠረፉ ፡ ፈቀቅ ፡ ብላ ፡ መጣች ። ጽኑ ፡ ነፋስ ፡ ተነሥቶ ፡ ስለ ፡ ነበር ፡ ታንኳይቱ ፡ ትንሳፈፍ ፡ ነበር ። ወዲያው ፡ ወደነርሱ ፡ መርከብ ፡ ተጠጋች ፤ ይህችኑ ፡ ታንኳ ፡ ሁለት ፡ ብላቴኖች ፡ ይቀዝፉዋት ፡ ነበር ።

፭ ፡ ወደ ፡ መርከቢቱ ፡ በተቃረቡ ፡ ጊዜ ፡ ከሁለቱ ፡ አንደኛው ፡ በጥሩ ፡ እንግሊዝ ፡ ቋንቋ ፡ «ገመድ ፡ አትወረውሩልንምን ፡ ወንድሞች» ፡ አለ ፤ ገመድ ፡ ወረወሩላቸውና ፡ ወደ ፡ መርከቡ ፡ እየተንጠላጠሉ ፡ ገቡ ።

፮ ፡ ወዲያው ፡ ሰር ፡ ቶማስ ፡ እስቴን ፡ እነማን ፡ እንደ ፡ ሆኑ ፤ ወደዚህስ እንዴት ፡ እንደመጡ ፤ በዚህ ፡ ደሴት ፡ እንዴት ፡ እንደሚኖሩ ፡ ቢጠይቃቸው ፡ ምስጢሩን ፤ ወዲያው ፡ ገለጡለት ።

፯ ፡ ክርስቲያንና ፡ ጓደኞቹ ፡ አታሂቲ ፡ የተባለችውን ፡ ደሴት ፡ በለቀቁ ፡ ጊዜ ፡ ፒትኪርን ፡ ወደ ፡ ተባለች ፡ ደሴት ፡ ሄዱ ። ወደ ፡ ጠረፉ ፡ በደረሱ ፡ ጊዜ ፡ ባውንቲ ፡

የተባለችውን ፡ የሸሹባትን ፡ መርከብ ፡ ከጠረፉ ፡ ላይ ፡ አቃጠሉዋትና ፡ ወደዚች ፡ ደሴት ፡ ገብተው ፡ ቤቶችን ፡ ሠርተው ፡ አቆሙ ። የወሰዱዋቸውን ፡ የአታሂቲን ፡ ሴቶች ፡ ሚስቶች ፡ አድርገው ፡ አገቡዋቸው ።

፳ ፡ ስሙ ፡ ጆን ፡ አዳም ፡ ከተባለ ፡ ከአንድ ፡ ሽማግሌ ፡ በቀር ፡ ክርስቲያንና ፡ ጓደኞቹ ፡ ሁሉ ፡ አልቀዋል ። ነገር ፡ ግን ፡ ልጆችና ፡ የልጅ ፡ ልጅ ፡ ተተዋልና ፡ አሁን ፡ ደሴቱ ፡ የሚበቁ ፡ ሕዝብ ፡ ስለ ፡ አሉበት ፡ ደሴቱ ፡ ደምቋል ።

፳፩ ፡ ሽማግሌው ፡ ጆን ፡ አዳም ፡ እውነቱን ፡ ለመግለጽና ፡ ወገኖቹም ፡ ቅንነትን ፡ እንዲጠብቁ ፡ ቅዱስ ፡ መጽሐፍን ፡ አስተማራቸው ። እጅግ ፡ ደስ ፡ ያላቸው ፡ ፍጥረቶች ፡ ይመስላሉ ። ኃጢአትና ፡ ኀዘን ፡ በዓለም ፡ ላይ ፡ መኖራቸውን ፡ አያውቁም ።

## ጥያቄ ።

፩ ፡ በ፲፰፻፫ ፡ ምን ፡ ተደረገ ፡ ?

፪ ፡ የፒካይርን ፡ ደሴት ፡ ወዴት ፡ ነው ፡ ? ምን ፡ ጊዜ ፡ ተገኘ ፡ ?

፫ ፡ በመርከቡ ፡ ላይ ፡ ሆኖ ፡ በመመልከት ፡ የታየው ፡ ምንድነው ፡ ?
ቤቶቹ ፡ ምን ፡ መስለው ፡ ይታዩ ፡ ነበር ፡ ?

፬ ፡ ከባሕሩ ፡ ጠረፍ ፡ የነበረው ፡ እንዴት ፡ ያለ ፡ ታንኳ ፡ ነው ፡ ?

፭ ፡ ታንኳዪቱን ፡ የሚቀዝፉ ፡ ምን ፡ ጉበዛዝት ፡ እንደ ፡ ነበሩ ፡ ተናገር ።
አሻግረው ፡ እየተጣሩ ፡ ምን ፡ አሉ ፡ ?

፮ ፡ ክርስቲያንና ፡ ጓደኞቹ ፡ አታሂቲን ፡ ለቀው ፡ ወዴት ፡ ሄዱ ፡ ?
በዚያ ፡ ምን ፡ አደረጉ ፡ ?

፯ ፡ ከሽፍቶቹ ፡ ማን ፡ ብቻ ፡ ቀረ ፡ ? በዚያ ፡ የቀሩት ፡ እንደምን ፡ እየተባዙ ፡ ሕዝብ ፡ ለመሆን ፡ በቁ ፡ ?
ጆን ፡ አዳም ፡ ለሕፃናቱ ፡ ምን ፡ አደረገላቸው ፡ ?

## ምዕራፍ ፡ ፳፯ ፡ አንታርክቲክ ።

፩ ፤ በሰሜን ፡ ወገን ፡ በአንታርክቲክ ፡ ውቅያኖስ ፡ አያሎች ፡ ደሴቶች ፡ እየተገኙ ፡ የደቡብ ፡ የብስ ፡ ተብለዋል ።

፪ ፤ ቢክቶሪያ ፡ የተባለው ፡ ደሴት ፡ በሺ ፡ ፲፰፻፵፩ ፡ ተገኘ ። የቢክቶሪያ ፡ ደሴት ፡ የተባለውም ፡ የታላቋን ፡ ብሪቴን ፡ ንግሥት ፡ ስለ ፡ ማክበር ፡ ነው ። ከጠረፉ ፡ በረድ ፡ የለበሰ ፡ በጣም ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ተራራ ፡ አለው ። ኤሬቡስ ፡ የተባለው ፡ ተራራ ፡ ቮልካኖ ፡ የሚወጣበት ፡ ነው ። ፲፪ሺ ፡ ፈት ፡ ከፍታ ፡ አለው ። በባሕር ፡ ላይ ፡ እንደሚያበራ ፡ መብራት ፡ ሆኖ ፡ በስፍራው ፡ ቁሞ ፡ ለዓለም ፡ ይታያል ። ነበልባሉ ፡ ከሚወጣበት ፡ ከጕድጓዱ ፡ አፍ ፡ ከሺ ፡ ፭፻ ፡ እስከ ፡ ፪ሺ ፡ ፈት ፡ ወደ ፡ ላይ ፡ ይነሣል ፡ ይባላል ። በድቅድቅ ፡ ጨለማ ፡ ሲያበራ ፡ ይታያል ። በምዕራብ ፡ ወገን ፡ ያለው ፡ የደቡብ ፡ ማግኔቲክ ፡ ፖል ፡ ነው ።

፫ ፤ ኬምፕና ፡ ኢንዲርቢ ፡ የተባሉት ፡ ደሴቶች ፡ ለማዳጋስካር ፡ ይቀርባሉ ። ሳብሪና ፡ ኤዴሊያ ፡ የሚባሉ ፡ አውራጃች ፡ በአውስትራልያ ፡ ደቡብ ፡ ናቸው ። ግሪሃም ፡ የተባለው ፡ አገር ፡ ፯፻ ፡ ማይል ፡ ለቴራዲል ፡ ፉጎ ፡ ይቀርባል ። በግሪሃም ፡ በደቡብና ፡ በደቡብ ፡ ምሥራቅ ፡ የሰሜን ፡ ሽትላንድ ፤ የደቡብ ፡ አርክኔ ፤ የደቡብ ፡ ጂዎርጂያን ፡ ደሴቶች ፡ ይገኛሉ ።

፬ ፤ በአፍሪካና ፡ በኙጂዎርጂያን ፡ ደሴቶች ፡ መካከል ፡ ትሪስታን ፤ ዳኩና ፡ የተባሉት ፡ ደሴቶች ፡ ያሉበት ፡ ነው ። እነዚህን ፡ ሰፊ ፡ ሁነው ፡ በአንድነት ፡ የተሰበሰቡ ፡ ደሴትች ፡ ታላቅ ፡ ብሪትን ፡ ተቈጣጥራአቸዋል ። ደሴቱ ፡ ሁሉ ፡ አፈር ፡ የሌለበት ፡ ጭንጫ ፡ ነው ። በነዚህም ፡ ላይ ፡ ከስምንት ፡ ሺ ፡ ፈት ፡ የበለጠ ፡ አሞጥሙጦ ፡ የወጣ ፡ ከፍታ ፡ አለ ። በነዚሁ ፡ ደሴቶችና ፡ በላፕላታ ፡ መካከል ፡ ፰ሺ ፡ ፫፻ ፡ ፋቶም ፡ (የባሕር ፡ ጥልቀት ፡ መስፈሪያ ፡ ) ጥልቅነት ፡ ያለው ፡ ውቅያኖስ ፡ ይገኛል ። ማለት ፡ ዘጠኝ ፡ ተኩል ፡ ማይል ፡ ርዝመት ፡ ነው ። ይኸም ፡ የተገኘበት ፡ በሺ ፡ ፲፰፻፺፱ ፡ ነው ።

፭ ፤ የፕሪንስ ፡ ኤድዋርድ ፡ ደሴቶች ፡ የተባሉት ፡ መልካም ፡ ተስፋ ፡ ከሚሉት ፡ አገር ፡ ከደቡብ ፡ ምሥራቅ ፡ ፯፻ ፡ ማይል ፡ ያህል ፡ ፈቀቅ ፡ ብለው ፡ ይገኛሉ ። ከነዚህም ፡ ደሴቶች ፡ ወደ ፡ ምሥራቅ ፡ ወገን ፡ ያሉት ፡ ክሮዜትና ፡ ማሪዎን ፡ የተባሉት ፡ ደሴቶች ፡ ናቸው ። አሁንም ፡ ደግሞ ፡ ወደ ፡ ምሥራቅ ፡ ራቅ ፡ ብሎ ፡ ኪርጉሊን ፡ የተባሉት ፡ ወይም ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ የተባሉት ፡ ደሴቶች ፡ ይገኛሉ ። እነዚህም ፡ ምንም ፡ ሊበቅልባቸው ፡ የማይችል ፡ አለቶች ፡ ናቸው ። ባንድ ፡ አንድ ፡ ስፍራ ፡ ግን ፡ ጐመን ፡ የሚመስል ፡ ነገር ፡ ያበቅላል ። ይህንንም ፡ ወደዚህ ፡ ጠረፍ ፡ የሚመጡ ፡ መርከበኞች ፡ ይወዱታል ። በሰሜን ፡ ምሥራቅ ፡ አምስተርዳምና ፡ የቅዱስ ፡ ጳውሎስ ፡ ደሴቶች ፡ አሉ ። ሁለቱም ፡ ፍል ፡ ውሃና ፡ ቮልካኖ ፡ የሚወጣበት ፡ ጕድጓድ ፡ አላቸው ። ይኸውም ፡ አሁን ፡ የባሕር ፡ መግቢያ ፡ ሆኖአል ።

፮ ፡ እነዚህ ፡ ደሴቶችና ፡ በአንታርክቲክ ፡ የሚገኙት ፡ መሬቶች ፡ ሁሉ ፡ ቮልካኖ ፡ ይበዛባቸዋል ። አልባትሮስ ፡ የሚባለው ፡ ታላቅ ፡ አሞራና ፡ ፒንጉዊን ፡ በዚያ ፡ በብዙ ፡ ይገኛሉ ። ዌልስ ፡ የሚሉት ፡ ዓሣነባሪ ፡ በዚያ ፡ ዙሪያ ፡ ሁሉ ፡ ይገኛል ።

፯ ፡ አንባቢዎች ፡ ሆይ ፤ የሚገኘው ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ ያለብዙ ፡ ድካምና ፡ ያለብዙ ፡ መከራ ፡ ያለብዙ ፡ ድፍረት ፡ እንዳልተገኘ ፡ ልታስቡ ፡ ይገባችኋል ። የተነገረው ፡ ሁሉ ፡ በጣም ፡ ትጋት ፡ ባላቸው ፡ መርከበኞች ፡ እንደ ፡ ተደረገ ፡ ተነግሮአል ። ሰር ፡ ጆን ፡ ፍራንክሊን ፡ የደረሰበትን ፡ መከራና ፡ ሞት ፡ እናስበው ። ጠፍተው ፡ የቀሩትን ፡ መርከቦች ፡ ለመፈለግ ፡ የተነሡትን ፡ ጀግኖች ፡ መርከበኞች ፡ እናስታውሳቸዋለን ። የፍራንክሊን ፡ ሚስት ፡ መከራ ፡ እናስበው ። ባልዋንና ፡ ጓደኞቹን ፡ ለማዳን ፡ ስንት ፡ ጊዜ ፡ እንደ ፡ ተጣጣረች ፤ ይህም ፡ አደጋ ፡ የሆነው ፡ በሰሜን ፡ በኩል ፡ ነበር ። ይኸውም ፡ ለመርከበኞች ፡ የደረሰባቸው ፡ ፍርሀትና ፡ መንቀጥቀጥ ፡ ጥፋትም ፡ ፍጹም ፡ በደቡብ ፡ በኩል ፡ በነበሩት ፡ መርከበኞች ፡ ላይ ፡ እንደ ፡ ደረሰባቸው ፡ ያለ ፡ አደጋ ፡ ነው ። በተቀረ ፡ ደግሞ ፡ የአየሩ ፡ ብርታት ፡ ሲከብዳቸው ፡ ውሃ ፡ ባነሰበት ፡ ስፍራ ፡ ተበረዶ ፡ ድንጋይ ፡ ጋር ፡ ሲታገሉና ፡ ሳያዩት ፡ እየቀሩ ፡ ስለሚያስቸግራቸው ፡ ታላቅ ፡ ጥንቃቄ ፡ ነበረባቸው ።

፰ ፡ ከሚያስፈራው ፡ አደጋ ፡ ሁሉ ፡ አንደኛውን ፡ ምንም ፡ ቢሆን ፡ በየብስ ፡ ላይ ፡ ለሚኖር ፡ ሰው ፡ ቢነግሩት ፡ ነገሩ ፡ አይገባውም ። እውነት ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ አይቀበለውም ። ይህም ፡ በወርኀ ፡ ጥቅምት ፡ በሺ ፡ ፰፻፹፫ ፡ ወደ ፡ ኖርትፖል ፡ ኤድዊንና ፡ ሊዚ ፡ የተባሉት ፡ መርከቦች ፡ በመድረሳቸው ፡ ታውቋል ። ካፒቴን ፡ ኪርክሀም ፡ እንዲህ ፡ ብለው ፡ ይተርኩልናል ። ስለ ፡ አንድ ፡ ታላቅ ፡ ልዩ ፡ የሆነ ፡ ዓሣነባሪ ፡ መርከቡን ፡ እንደመታው ፤ አመታቱም ፡ ታላቅ ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ ይናገራል ።

፱ ፡ ይህም ፡ መርከብ ፡ ሣንቃ ፡ እንደ ፡ ተጫነ ፡ የፕሬንስ ፡ ኤድዋርድ ፡ ደሴት ፡ በተባለው ፡ ጠረፍ ፡ ቀረ ። በ፲፱ኛ ፡ ጥቅምት ፡ ሌላ ፡ ትልቅ ፡ ዓሣነባሪ ፡ መርከቡን ፡ መታው ። ኤድዊንና ፡ ሊዚን ፡ የሚባሉትን ፡ የመርከቦችን ፡ መሪ ፡ ጫፍ ፡ ሰብሮ ፡ ወሰደው ። የቀረውም ፡ ዋናው ፡ የመርከቡ ፡ ክፍል ፡ ከሁለት ፡ ተሠነጠቀ ።

፲ ፡ በዚህ ፡ ሁኔታ ፡ ምክንያት ፡ በመርከቡ ፡ ላይ ፡ ጩኸትና ፡ ሁከት ፡ ሆነ ። ምናልባት ፡ መርከበኞችንና ፡ መርከቡን ፡ ለማዳን ፡ ይቻል ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ብማለት ፡ በፍጥነት ፡ አጋጠሙት ፡ ውሃውን ፡ ሌሊትና ፡ ቀን ፡ ሳያቋርጡ ፡ በፖምፕ ፡ አወጡት ። ኤድዊንና ፡ ሊዚ ፡ መርከቦቹ ፡ ሰበት ፡ ፊት ፡ ያህል ፡ ከውሃው ፡ ውጭ ፡ ነበሩ ። በኋላም ፡ መርከብ ፡ ወደሚቆምበት ፡ በደኅና ፡ ደረሱ ።

፲፩ ፡ መርከቡ ፡ የጫነው ፡ እስኪራገፍ ፡ የቱን ፡ ያህል ፡ እንደ ፡ ተጐዳ ፡ ገና ፡ አርግጡ ፡ አልታወቀም ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን ፡ ከመስጠም ፡ መዳኑ ፡ ታወቀ ። ለካፒቴን ፡ ኪርክሀምና ፡ ለሹሞቹ ፡ ለመርከበኞቹም ፡ ብዙ ፡ ምስጋና ፡ ብቻ ፡ አይበቃቸውም ። መርከቦቹ ፡ ወደ ፡ ባሕር ፡ እንዳይሰጥሙ ፡ ፲፱ ፡ ቀን ፡ ሙሉ ፡ ሌሊቱንም ፡ ቀኑንም ፡ ሠርተዋል ። ይህን ፡ ያህል ፡ ድካም ፡ ባይደረግላቸው ፡ ኖሮ ፡ ቢሆን ፡ መርከቦቹ ፡ ተበላሽተው ፡ ይቀሩ ፡ ነበር ።

ጥ ያ ቄ ።

፩ ፤ ፈት ፡ ለተገኙት ፡ የብሶች ፡ ምን ፡ ስም ፡ ተሰጣቸው ፡ ?
፪ ፤ ስለ፡ቢክቶሪያ፡ላንድ፡ተናገር ። ኤሬቡስ ፡ ስለተባለው ፡ ተራራ፡ ተናገር።
በምዕራብ ፡ በኩል ፡ ወገን ፡ ያለው ፡ ምንድነው ፡ ?
፫ ፤ ኪምፕና ፡ ኤንደርቢ ፡ ላንድ ፡ ያሉት ፡ በወዴት ፡ ወገን ፡ ነው ? ግራ
ሀምላንድ ፡ ወዴት ፡ ነው ፡ ?
በሰሜንና ፡ በሰሜን ፡ ምዕራብ ፡ ያሉት ፡ ደሴቶች ፡ ማን ፡ የሚባሉ ፡
ናቸው ፡ ?
፬ ፤ ትሪስታን ፡ ዳኩና ፡ የተባለው ፡ ደሴት ፡ ወዴት ፡ ነው ፡ ? የባሕሩ፡ ጥል
ቅነት ፡ የቱን ፡ ያህላል ፡ ?
፭ ፤ የፕሪንስ ፡ ኤድዋርድ ፡ ደሴቶች ፡ ያሉት ፡ ወዴት ፡ ነው ፡ ?
በምሥራቅ ፡ ወገን ፡ ያሉ ፡ ደሴቶች ፡ ማን ፡ ይባላሉ ፡ ? ከርጉሊን ፡
የተባሉት ፡ ደሴቶች ፡ ምንድናቸው ፡ ?
አምስተርዳምና ፡ ሴንት ፡ ጳውሎስ ፡ የተባሉ ፡ ደሴቶችስ ፡ ?
፮ ፤ በአንታርክቲክ ፡ እንዴት ፡ ያሉ ፡ ወፎችና ፡ እንስሶች ፡ ይገኛሉ ፡ ?
፯ ፤ መርከበኞችና ፡ መርማሮች ፡ ክፉን ፡ ለመጠበቅ ፡ ሲሉ ፡ እንዴት ፡ ያለ ፡
አደጋ ፡ አገኛቸው ፡ ?
፰ ፤ ኤድዊንና ፡ ሊዚ ፡ እንደምን ፡ ሆኑ ፡ ?
፱ ፤ ስለ ፡ ሆነው ፡ አደጋ ፡ ካፒቴን ፡ ምን ፡ ተረከ ፡ ?
፲ ፤ መርከበኞች ፡ ምን ፡ አደረጉ ፡ ?
፲፩ ፤ ለማን ፡ ምስጋና ፡ ተደረገ ፡ ? ማን ፡ ተመሰገነ ፡ ?

---

## ምዕራፍ ፡ ፪፻፫ ፡ ፪ኛ ፡ እንደ ፡ ገና ፡ መመርመር ።

### በእስያና ፡ በአፍሪካ ፡ የመንግሥታት ጥንታዊነት ።

፩ ፤ ያራቱን ፡ መዓዝነ ፡ ዓለምን ፡ ታሪክና ፡ አሺያኒያ ፡ የተባለውን ፡ ያምስተኛው ንም ፡ የዓለም ፡ ክፍል ፡ ጨምሬ ፡ ነግሬአችኋለሁ ። እስቲ ፡ ወደ ፡ ኋላችን ፡ ገል መጥ ፡ ብላን ፡ በውስጣቸው ፡ እየሄድን ፡ ያለፍናቸውን ፡ አገሮችና ፡ ዋና ፡ ዋና የሆነውን ፡ ታሪክ ፡ እናስታውሰው ።

፪ ፤ የዓላም ፡ ፍጥረት ፡ ተክርስቶስ ፡ ልደት ፡ በፊት ፡ ፭ሺ ፡ ፭፻ ፡ ዘመን ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ ትዝ ፡ ሳይላችሁ ፡ አይቀርም ። ይኸው ፡ አሁንም ፡ ከክርስቶስ ፡ ልደት ፡ ወዲህ ፡ ሺ ፡ ፱፻፵፮ ፡ ዓመት ፡ እንደ ፡ ሆነ ልብ ፡ ታደርጉት ፡ ይሆናል ። እንዲህ ከሆነ ፡ ዓለም ፡ ከተፈጠረ ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡ ፯ሺ ፡ ፬፻፵፮ ፡ ዓመት ፡ መሆኑ ፡ ነው ።

፫ ፤ ዓለም ፡ እንዴት ፡ ያለውን ፡ ታሪክ ፡ ያሳያል ፡ ! ከዛሬ ፡ ፫ ሺሕ ፡ ዓመት ፡ በፊት ፡ ከዚህም ፡ ጥቂት ፡ ዘመኑ ፡ አነስ ፡ ሳይል ፡ አይቀርም ። በዓለም ፡ ላይ ፡ ሁለት ፡ ሰዎች ፡ ብቻ ፡ ይኖሩ ፡ ነበሩ ። በሌላው ፡ ዓለም ፡ ክፍል ፡ ሁሉ ፡ ምንም ሰው ፡ አልነበረበትም ። አሁን ፡ ግን ፡ መላው ፡ ዓለም ፡ በሰው ፡ ተመልቶአል ። (ሰው ፡ መልቶበታል ። ) በዓለም ፡ ያለውም ፡ ሕዝብ ፡ ምንም ፡ ቢያንስ ፡ ከአንድ ፡ ሺሕ ፡ ሚሊዮን ፡ አያንስም ።

፬ ፤ አዳምና ፡ ሔዋን ፡ ከተፈጠሩ ፡ ወዲህ ፡ ስንትና ፡ ስንት ፡ ነገድ ፡ እየተነሡ ፡ ደግሞ ፡ አለፉ ፡ ? ስንትና ፡ ስንት ፡ ነገሥታት ፡ (መንግሥታት ፡) እየገነኑ ፡ እን ደገና ፡ ደግሞ ፡ ተመልሰው ፡ ጠፉ ፡ ? በሕይወት ፡ የነበሩትና ፡ የሞቱት ፡ ስንት ፡ ሚሊዮን ፡ የሚሆኑ ፡ ሕዝብ ፡ ነበሩ ፡ ? ይህን ፡ ከቶ ፡ እኛ ፡ ልንቈጥረው ፡ የማ ይቻል ፡ ነው ።

ነገር ፡ ግን ፡ ዓለም ፡ ከተፈጠረ ፡ ጀምሮ ፡ ያለውም ፡ የሞተውም ፡ ሰው ፡ ምን አልባት ፡ ምንም ፡ ቢያንስ ፡ አንድ ፡ መቶ ፡ ሺህ ፡ ሚሊዮን ፡ ሳይሆን ፡ አይቀርም ።

፭ ፤ ነገሩን ፡ ስናስበው ፡ እጅግ ፡ ሰፊ ፡ ነው ። ነገር ፡ ግን ፡ ታሪክ ፡ የሚሰጠንን አሳብ ፡ ተከትለን ፡ አሳባችንን ፡ ወደዋናዎች ፡ መንግሥታት ፡ እንመልስ ። ልብ እንደምታደርጉት ፡ መጀመርያ ፡ መንግሥት ፡ የሆነ ፡ አሶር ፡ ነበረ ። ይህም ፡ ተክር ስቶስ ፡ ልደት ፡ በፊት ፡ ፪ሺ ፡ ፪፻፳፱ ፡ አሶር ፡ መሠረተው ። ተክርስቶስ ፡ ልደት ፡ በፊት ፡ ፱፻ ፡ ዓመት ፡ ሲሆን ፡ አርባስስ ፡ ገለበጠው ። ነገር ፡ ግን ፡ ይህ ፡ ከሆነ ፡ በኋላ ፡ እን ደገና ፡ ተጠናከረና ፡ ተክርስቶስ ፡ ልደት ፡ በፊት ፡ ፭፻፴፰ ፡ እስከ ፡ ቂሮስ ፡ ዘመን ፡ ድረስ ፡ ጸንቶ ፡ ቈየ ። ከመጀመርያ ፡ አንሥቶ ፡ እስከ ፡ መጨረሻ ፡ መገልበጥ ፡ ድረስ ፡ የነበረው ፡ ዘመን ፡ መንግሥቱ ፡ ሺ ፡ ፯፻፺፩ ፡ ዓመት ፡ ነው ።

፮ ፤ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ ታላቅ ፡ መንግሥት ፡ የሚባለው ፡ የፋርስ ፡ መንግሥት ፡ ነው ። ይህም ፡ ተክርስቶስ ፡ ልደት ፡ በፊት ፡ ፭፻፴፮ ቂሮስ ፡ መሠረተው ። ይህም ፡

ታላቅ ፣ መንግሥት ፣ ሆነና ፣ በጣም ፣ ተንሰራፍቶ ፣ ብዙውን ፣ የእስያን ፣ ክፍል ያዘው ። ነገር ፣ ግን ፣ ተክርስቶስ፣ ልደት፣በፊት ፣ ፫፻፴ ፣ አለክሳንድር ድል ፣ አደ ረገው ። ፪፻፳፮ ፣ ዓመት ፣ ከቈየ ፣ በኋላ ፣ ወዲያው ፣ ለፓርቲያን ፣ ተገዛ ። የዛሬው የፋርስ ፣ መንግሥት ፣ በስፋት ፣ እጅግ ፣ ትንሽ ፣ ነው ።

፯ ፤ እንደ፣ቻይን፣አድርጎ ፣ብዙ ፣ ሕዝብ ፣ ያለው ፣ መንግሥት ፣በዓለም ፣ አይገኝም ። ደግሞም ፣ ጥንታዊ ፣ መንግሥት ፣ ነው ። ቺን ፣ ከመጀመርያው ፣ ንጉሥ ፣ ነገ ሥቱ ፣ ጀምሮ ፣ እስከ ፣ ዛሬ ፣ ድረስ ፣ ፬ሺ ፣ ዓመት ፣ ያህል ፣ ሆኖታል ። የሳራ ፊን ፣ መንግሥት፣የተጀመረው ፣ ተክርስቶስ ፣ ልደት ፣ በኋላ ፣ ፭፻፬፫ ፣ ዓመት ፣ ነው ። ተክርስቶስ ፣ ልደት ፣ በኋላ ፣ ሺ፪፻፶፫ ፣ መንግሥቱን ፣ ቱርክ ፣ ገለበጠ ውና ፣ ወዲያው ፣፯፻፷ ፣ ዓመት ፣ እንደያዘው ፣ ኖረ ።

፰ ፤ የአይሁድ ፣ ሕዝብ ፣ ታሪክ ፣ ከአብርሃም ፣ እንደ፣ተጀመረ ፣ ይታሰባል ። እር ሱም ተክርስቶስ ፣ ልደት፣በፊት፣ሺ፱፻፹፮ ፣ ከልድያን፣ትቶ፣ወደ ፣ ከነዓን ፣ ሄደ ። ከዚህ፣ ዘመን ፣ ጀምሮ ፣ ኢየሩሳሌም ፣ በቲቶስ ፣ እስከ ፣ ጠፋበት ፣ ድረስና ፣ አይሁድ፣እስከ፣ተበተኑበት፣ተክርስቶስ ፣ልደት ፣ በኋላ ፣ እስከ፣ሰባ ፣ ዓመት ፣ ድረስ በመካከል ፣ ያለው ፣ ዘመን ፣ ፩ሺ ፱፻፺፮፣ዓመት ፣ ነበር ። እስራኤል ፣ ከምስር ፣ ከወጡበት ፣ ዘመን ፣ ጀምሮ ፣ ኢየሩሳሌም ፣ ከጠፋች ፣ በኋላ ፤ እስከ ፣ አይሁድ ፣ መበተን ፣ ድረስ ፣ የነበረው ፣ ዘመን ፣ ሺ፭፻፹፮ ፣ ዓመት ፣ ነበር ። ባጭሩ ፣ የሚ ታዩ ፣ ታላላቆች ፣ የእስያ ፣ መንግሥታት ፣ እነዚህ ፣ ናቸው ።

፱ ፤ ብዙ ፣ ዘመን ፣ የኖረ ፣ የአፍሪካ ፣ መንግሥት ፣ ምስር ፣ ብቻ ፣ ነው ። ይህም ተክርስቶስ ፣ ልደት በፊት ፣ ፪ሺ፣፭፻፹፫፣ሚስራይም ፣ መሠረተውና ፣ ተክርስቶስ ፣ ልደት ፣ በፊት ፣ ፫፻፴፪ ፣ እስከ ፣ ነበረው ፣ እስከ ፣ እስክንድር ፣ ዘመን ፣ ድረስ ፣ ጸንቶ ፣ ኖረ ። በዚህ ፣ ጊዜ ፣ ፩ሺ ፣፫፻፶፯ ፣ ዘመን ፣ ያህል ፣ ብዙ ፣ መለዋወጥ ፣ ተደርጓል ። ስለ፣ሆነ፣ጸንቶ ፣የኖረ ፣ አንድ ፣ መንግሥት ፣ ተብሎ ፣ ይታሰባል ። እስክንድር ፣ ድል ፣ አድርጎ ፣ ከያዘው ፣ ወዲህ ፣ አያሎች ፣ ገዝተውታል ።

፲ ፤ ጥንት ፣ ካርታጎ ፣ የፈኒቅያኖች ፣ ቅኝ ፣ ነበር ። ተክርስቶስ ፣ ልደት ፣ በፊት ፣ ፰፻፹፱ ፣ ዓመት ፣ ተመሠረተ ። ሕዝቡ ፣ ብዙ ፣ መርከቦች ፣ ነበሩዋቸው ። በሚዲ ቴራኒያን ፣ባሕር ዙሪያ ፣ ባሉት ፣ ከተሞች ፣ ሁሉ ፣ ይነግዱ ፣ ነበርና ፣ በእስጴንና ፣ በአፍሪካ ፣ ጠረፍ ፣ ሁሉ ፣ የቅኝ ፣ አገሮችን ፣ መሠረቱ ።

፲፩ መርከቦቻቸውም ፣ ወደ ፣ ሩቅ ፣ አገር ፣ ይንሳፈፉ ፣ ነበር ። ግማሾቹም ፣ ወደ አትላንቲክ ፣ ውቅያኖስ ፣ እየሄዱ ፣ የምዕራብ ፣ አፍሪካን ፣ ይጐበኙ ነበር ። መር ከቦቻቸው ፣ እንዲያው ፣ በመላው ፣ አትላንቲክ ፣ ውቅያኖስን ፣ ተሻግረው ፣ አሜ ሪካን ፣ አገኙና ፣ መኖሪያቸውን ፣ በዚያው ፣ አደረጉ ። በዚያም ፣ ከጥንት ፣ የነበሩ ትን ፣ ነገዶ ፣ ህንድ ፣ አገኙዋቸው ። ይህም ፣ እውነት ፣ ነው ።

፲፪ ፤ የሆነ ፤ ሆኖ ፣ ካርታጎ አንድ ፣ ጊዜ ፣ እጅግ ፣ የገነነች ፣ ከተማ ፣ ሁና ፣ ነበር ። በዙሪያዋም ፣ ባሉት ፣ አህጉር ፣ ያለመጠን ፣ ሕዝቡ ፣ በዝቶ ፣ ይጋፋ ፣ ነበር ። የሮም

ተፎካካሪ ፡ ለመሆን ፡ እስክትበቃ ፡ ኀይል ፡ ነበራት ። ከትዕቢተኛው ፡ ተፎካካሪዋ
ጋር ፡ ብዙ ፡ ግጭት ፡ ተደርጓል ። ፯፻፷፫ ፡ ዓመት ፡ ከኖረች ፡ በኋላ ፡ ተክርስቶስ ፡ ልደት ፡
በፊት ፡ በ፻፵፮ ፡ ዓመት ፡ በመጨረሻው ፡ ትግል ፡ መንግሥቱዋ ፡ ተገለበጠ ፡ ( ተሻረ ) ።
፲፫ ፤ (የአራዊት ፡ ) ያረመኔ ፡ መንግሥታት ፡ የተባሉ ፡ ሞሮኮ ፤ አልጀር ፤ ትሪፖሊ
ቱኒስ ፡ ናቸው ። እነዚህ ፡ በኋላ ፡ የተነሡ ፡ ናቸው ። ፊት ፡ እንደ ፡ ተናገርሁ ፡ በነ
ዚህ ፡ አገሮች ፡ ውስጥ ፡ ሰው ፡ የገባባቸው ፡ በሮማውያን ፡ ጊዜ ፡ ነው ። ባገሩ ፡
ብዙ ፡ ሕዝብ ፡ የገባበት ፡ ይመስላል ፤ ሁሉም ፡ ለሮም ፡ ተገዝተዋል ። ሳራሴኖች ፡
አገሩን ፡ እስኪይዙት ፡ ድረስ ፡ ብዙ ፡ መለዋወጥ ፡ ሆኖ ፡ ነበር ። በኋላኛው ፡ ዘመን
ለቱርክ ፡ ተገዙ ። ይኸውም ፡ ቢሆን ፡ ነጻነት ፡ አላገኙም ። አሁንም ፡ ቢሆን ፡
አልጀር ፡ ለፈረንሳይ ፡ መንግሥት ፡ ይገዛል ።

## ጥ ያ ቄ ።

፩ ፤ ዓለም ፡ ምን ፡ ጊዜ ፡ ተፈጠረ ፡ ? ክርስቶስ ፡ ከተወለደ ፡ ምን ፡ ያህል ፡
ዓመት ፡ ሆነ ፡ ?
ዓለም ፡ ከተፈጠረ ፡ ምን ፡ ያህል ፡ ዘመን ፡ ሆነ ፡ ?
፪ ፤ የዛሬ ፡ ፯ሺ ፡ ዓመት ፡ ዓለም ፡ እንደምን ፡ ነበር ፡ ?
አሁንሳ ፡ እንዴት ፡ ነው ፡ ?
፫ ፤ ዓለም ፡ ከተፈጠረ ፡ ወዲህ ፡ ያለው ፡ ስንት ፡ ሕዝብ ፡ ይሆን ፡ ?
፬ ፤ የአሶርን ፡ መንግሥት ፡ ማን ፡ መሠረተው ፡ ? የተመሠረተውስ ፡ ምን ፡
ጊዜ ፡ ነው ፡ ?
እንደምን ፡ ኖረ ፡ ? አንዋንዋሩ ፡ እንደምን ፡ ነበር ፡ ?
፭ ፤ የፋርስ ፡ መንግሥን ፡ እንደምን ፡ ሆነ ፡ ?
ቺን ፡ እንዴት ፡ ሆነ ፡ ?
፮ ፤ የሳራሴን ፡ መንግሥት ፡ እንዴት ፡ ሆነ ፡ ?
፯ ፡ የአይሁድ ፡ ሕዝብ ፡ እንዴት ፡ ሆኑ ፡ ?
፰ ፤ ግብጾችስ ፡ ?
፲ ፡ ካርታጎ ፡ ምን ፡ ጊዜ ፡ ተመሠረተ ፡ ? ፊኒቂያኖችስ ፡ እንዴት ፡ ሆኑ ፡ ?
፲፩ ፤ መርከቦቻቸውስ ፡ ? መርከበኞቻቸውስ ፡ ?
፲፪ ፤ ካርታጎ ፡ እንደምን ፡ ሆነ ፡ ? የተገለበጠውስ ፡ ምን ፡ ጊዜ ፡ ነው ፡ ?
ምን ፡ ያህል ፡ ጊዜ ፡ ኖሮ ፡ ነበር ፡ ?
፲፫ ፤ የአራዊት ፡ ሕዝብ ፡ መንግሥት ፡ እንዴት ፡ ነው ፡ ?
፲፬ ፤ አልጀሮች ፡ እንደምን ፡ ሆኑ ፡ ?

## ምዕራፍ ፡ ፪፻፲ ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ምርመራ ።

### የመንግሥታት ፡ ጸንቶ ፡ መኖር ፡ በኤውሮጳ ።

፩ ፤ እስቲ ፡ አሁን ፡ ወደ ፡ ኤውሮጳ ፡ እንመለስ ፤ ኬልቶች ፡ የተባሉት ፡ ሕዝብ ፡ ጥንት ፡ ዘመን ፡ ከእስያ ፡ ተነሥተው ፡ ወደ ፡ ኤውሮጳ ፡ የፈለሱ ፡ ይመስላል ። በደቡብ ፡ ምዕራብ ፡ ወገን ፡ በጥቍር ፡ ባሕርና ፡ በካስፒያን ፡ ባሕር ፡ መኻከል ፡ አልፈውም ፡ እንደ ፡ ሆኑ ፡ ወይም ፡ የዑራልን ፡ ተራራ ፡ አልፈው ፡ በካስፒያን ፡ ባሕር ፡ ሰሜን ፡ አድርገው ፡ ተሻግረው ፡ እንደ ፡ ሆኑ ፡ ለመናገር ፡ አልችልም ።

፪ ፤ ተክርስቶስ ፡ ልደት ፡ በፊት ፡ ፬ሺ ፡ ዓመት ፡ የተበታተኑ ፡ ነገድ ፡ ጥንት ፡ ዘመን ፡ ወደ ፡ መኻከል ፡ ኤውሮጳ ፡ ገብተው ፡ ያሆናል ፡ ተብሎ ፡ መላ ፡ ተደርጓል ። ዳሩ ፡ ግን ፡ ነገሩ ፡ እውነት ፡ ይመስላል ። በጀርመን ፤ በፈረንሳይ ፤ በኢጣልያ ፡ ሰሜን ፡ በብሪቴን ፡ የገቡት ፡ እጅግ ፡ ብዙ ፡ ነበሩ ። ወደነዚህ ፡ አገሮች ፡ የገቡትም ፡ ተክርስትና ፡ በፊት ፡ ካያል ፡ መቶ ፡ ዘመናት ፡ በፊት ፡ ነው ።

፫ ፤ ኬልቶች ፡ መጀመርያ ፡ ወደ ፡ ኤውሮጳ ፡ የገቡበት ፡ ዘመንና ፡ መቼም ፡ ቢሆን ፡ በዚያ ፡ የዓለም ፡ ክፍል ፡ ሰው ፡ መጀመርያ ፡ የገባው ፡ ፊኒቂያኖች ፡ ተክርስቶስ ፡ ልደት ፡ በፊት ፡ ፩ሺ ፡ ፰፻፶፮ ግሪክን ፡ ቅኝ ፡ አድርገው ፡ ሲይዙት ፡ ነው ። የዚሁም ፡ ቅኝ ፡ አገር ፡ መሪ ፡ ኢናኩስ ፡ ይባላል ።

፬ ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ከዚያ ፡ በኋላ ፡ አቴንን ፡ ሴክሮብስ ፡ እስቲመሠርታት ፡ ድረስ ፡ ሦስት ፡ መቶ ፡ ዓመት ፡ አልቈየም ፡ ይህም ፡ ሴክሮብስ ፡ በዚያ ፡ ለመኖር ፡ የፈለጉትን ፡ አያሎች ፡ ግብጻውያንን ፡ ይዞ ፡ ወደዚህ ፡ የመጣ ፡ ነው ። ይህም ፡ የግሪክች ፡ መንግሥት ፡ መሠረት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ይታሰባል ። የግሪኮችም ፡ ታሪክ ፡ መጀመርያ ፡ ከዚህ ፡ ላይ ፡ ነው ።

፭ ፤ ኢናኩስ ፡ ግሪክን ፡ በያዘ ፡ በሺ ፡ ፰፻፲ ፡ ዓመት ፡ ሴክሮፕስ ፡ አቴንን ፡ በመሠረተ ፡ በሺ ፡ ፭፻፲ ፡ ዓመት ፡ ተክርስቶስ ፡ ልደት ፡ በፊት ፡ ፻፵፮ ፡ ዓመት ፡ የግሪኮች ፡ ነጻነት ፡ በሮማውያን ፡ ማሸነፍ ፡ ተወሰነ ።

፮ ፤ ተክርስቶስ ፡ ልደት ፡ በፊት ፡ ፯፻፶፫ ፡ የሮም ፡ መንግሥት ፡ ተመሠረተ ። መላው ፡ የሠለጠነው ፡ ዓለም ፡ ተጐንብሶ ፡ በቀንበሩ ፡ እስቲጠመድ ፡ ድረስ ፡ የሮም ፡ መንግሥት ፡ ኀይሉና ፡ ብርታቱ ባለማቋረጥ ፡ እየገነነ ፡ ሄደ ። የመንግሥቱ ፡ ሁኔታ ፡ መቼውንም ፡ ይለዋወጣል ። መጀመርያ ፡ ንጉሥ ፡ ቀጥሎ ፡ ፕሬዚዳንት ፡ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ (ቄሣር) በማለት ፡ ይታያል ። በ፬፻፸፮ ፡ ዓ. ም. የሮምን ፡ ከተማ ፡ ኦዳስር ፡ የተባለ ፡ ያዛት ። ዘመኑ ፡ በግዛቱ ፡ ይታወቃል ። የሮም ፡ መንግሥት ፡ ዘመን ፡ በመላው ፡ ፩ሺ ፪፻፳፱ ዓመት ፡ መሆኑ ፡ ነው ።

፯ ፤ ዋና ፡ ከተማው ፡ ቢዛንቲውም ፡ በኋላም ፡ ክስታንቲኖፕል ፡ (ቍስጥንጥንያ ፡) የተባለው ፡ ነው ። የግሪክ ፡ መንግሥት ፡ ጥንት ፡ የሮም ፡ መንግሥት ፡ ክፍል ፡ ነበር ። ይኸውም ፡ የምሥራቅ ፡ መንግሥት ፡ ተብሏል ። በ፲፬፻፶፫ ፡ ዓ. ም. ቈስጠንጢኖስ ፡ ዋና ፡ ከተማውን ፡ በቍስጥንጥንያ ፡ በአደረገ ፡ ጊዜ ፡ የግሪክ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ አገር ፡ ተጀመረ ።

፰ ፤ እስከ ፡ ሺ ፡ ፬፻፶፫ ፡ ዓ. ም. ልዩ ፡ ልዩ ፡ ፈተና ፡ ተደርጎ ፡ ቱርኮች ፡ ቍስጥንጥ ያን ፡ በያዙ ፡ ጊዜ ፡ የግሪክ ፡ መንግሥት ፡ ሺ ፡ ፻፳ ፡ ዓመት ፡ ሆኖት ፡ ነበር ።

፱ ፤ የሳራሴን ፡ መንግሥት ፡ ሲጨረስ ፡ የቱርክ ፡ መንግሥት ፡ መጀመርያ ፡ ይታ ያል ። በሺ ፡ ፶፻፶፫ ፡ ዓ. ም. ቱርኮች ፡ ታርታሮች ፡ ተብለው ፡ የሳራሴንን ፡ መን ግሥት ፡ ገለበጡና ፡ የመሐመድን ፡ ሃይማኖት ፡ ተቀብለው ፡ በዚሁ ፡ ኖሩ ፡ መንግ ሥታቸውንም ፡ ሳራሴኖች ፡ ድል ፡ አድርገው ፡ በያዙዋቸው ፡ አገሮችና ፡ በሌሎ ችም ፡ አውራጆች ፡ አንሳፈፉ ።

፲ ፤ አንደኛ ፡ ኦቶማን ፡ የተባለ ፡ በሺ ፡ ፪፻፺፱ ፡ ነገሠና ፡ በሺ ፡ ፫፻፱ ፡ የኦቶማ ንን ፡ መንግሥት ፡ መሠረተ ። እስከ ፡ ዛሬም ፡ አለ ። ስለዚህ ፡ የቱርክ ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ፡ በሺ ፡ ፪፻፶፰ ፡ ከተደረገው ፡ ከባግዳድ ፡ ማሸነፍ ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ፩ሺ ፡ ፱፻፳ ፡ ድረስ ፡ ፮፻፷፪ ፡ ዓመት ፡ መሆኑ ፡ ነው ። የኦቶማን ፡ ዘመነ ፡ መንግ ሥት ፡ ኦቶማን ፡ ፩ኛ ፡ ከመሠረተው ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ፩ሺ ፡ ፱፻፳ ፡ ድረስ ፮፻፳፩ ፡ ዓመት ፡ መሆኑ ፡ ነው ። በሺ ፡ ፬፻፶፫ ፡ ዓ. ም. ኮስታንቲኖፕልን ፡ ቱርክ ፡ ከያዘው ፡ ጀምሮ ፡ ያች ፡ ስፍራ ፡ የኦቶማን ፡ መንግሥት ፡ ዋና ፡ ከተማ ፡ ነች ።

፲፩ ፤ የፈረንሳይ ፡ መንግሥት ፡ በቺልዴሪክ ፡ ተጀመረ ። እርሱም ፡ በ፬፻፶፯ ፡ ነገሠ ። ክሎቪስ ፡ የተባለ ፡ ልጁ ፡ መጀመርያ ፡ የክርስቲያን ፡ ንጉሥ ፡ ሆነና ። ሮማውያ ንን ፡ ከፈረንሳይ ፡ አገር ፡ አስወጣቸው ። ስለዚህ ፡ የፈረንሳይ ፡ መንግሥት ፡ ዘመ ኑን ፡ ሲቈጥር ፡ በ፬፻፹፩ ፡ ዓ. ም. አባቱን ፡ ቺልዴሪክን ፡ ከወረሰበት ፡ ቀን ፡ ይጀም ራል ። ስለዚህ ፡ የፈረንሳይ ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ፡ ከ፬፻፹፩ ፡ እስከ ፡ ፩ሺ፯፻፹፩ ፡ ያለው ፡ ፩ሺ ፡ ፫፻፱ ፡ ዓመት ፡ መሆኑ ፡ ነው ። ከኤውሮጳ ፡ ውስጥ ፡ አንዱ ፡ ጥን ታዊ ፡ መንግሥት ፡ ይኸው ፡ ነው ።

፲፪ ፤ የእንግሊዝም ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ፡ በኤግበርት ፡ ይጀምራል ። እርሱም ፡ የመጀመርያ ፡ የሳክሶን ፡ ንጉሥ ፡ ነው ።
በ፰፻፳፯ ፡ ዓ. ም. በዙፋን ፡ ተቀመጠ ። ከዚህ ፡ ዘመን ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ፩ሺ ፡ ፱፻፳ ፡ ዓ. ም. ፡ ያለው ፡ ዘመን ፡ ሺ፺፫ ፡ ዓመት ፡ መሆኑ ፡ ነው ። ከፈረንሳይ ፡ ቀጥሎ ፡ በኤውሮጳ ፡ አንዱ ፡ የኖረ ፡ መንግሥት ፡ የሚባለው ፡ ይህ ፡ ነው ።

፲፫ ፤ ሌሎቹ ፡ የኤውሮጳ ፡ መንግሥታት ፡ በኋላ ፡ የተነሡ ፡ ናቸው ። ሙርስ ፡ (ሞርኮ) የተባሉት ፡ መንግሥታቸውን ፡ መጀመርያ ፡ በእስጴን ፡ ያቆሙት ፡ በ፯፻፲፪ ፡ ዓ. ም. ነበር ። በዚያ ፡ አገር ፡ መንግሥት ፡ አቁመው ፡ ፯፻፹ ፡ ዓመት ፡ ከገዙ ፡ በኋላ ፡ በሺ ፬፻፺፪ ዓ. ም. አስወጡዋቸው ። አገሩ ፡ እስጴን ፡ አራት ፡ ተከፍሎ ፡ ሦስቱን ፡ እጅ ፡ ሙሮች ፡ ብዙ ዘመን ፡ ይገዙት ፡ ነበር ። ዳሩ ፡ ግን ፡ የቀረው ፡ ነጻ ፡ ነበርና ፡ የነጉሥ ፡ አገር ፡ ተብሎ ፡ ይኖር ፡ ነበር ። ከነዚህም ፡ አንዱ ፡ አስቱሪያስ ፡ ያባላል ። የመሠረተው ፡ ፔልጂዮ ፡ ይባላል ። የርሱ ፡ ወራሾች ፡ ከሲቲሊን ፤ ሊዎንን ፡ አር ጐንና ፡ ሌሎችንም ፡ መንግሥቶች ፡ መሠረቱ ።

፲፬ ፤ ፌርዲናንድ ፡ የተባለ ፡ የአራጎን ፡ ንጉሥ ፡ በሺ ፡ ፬፻፸፱ ፡ ዓ. ም. ነገሠና ፡ ኢዛቤ

ላን ፡ የካስቲሌን ፡ ንግሥት ፡ ስለ ፡ አገባ ፡ የሁለቱም ፡ መንግሥት ፡ በንድነት ፡ ተጋጠመ ። ከዚህ ፡ ጊዜ ፡ ጀምሮ ፡ አያሎች ፡ የእስጳንያ ፡ ክፍሎች ፡ ጥቂት ፡ በጥቂት ፡ እያሉ ፡ አንድ ፡ መንግሥት ፡ መሆን ፡ ጀመሩ ። ስለዚህ ፡ የፌርዲናድን ፡ መንገሥ ፡ መጀመርያ ፡ የእስጳንያ ፡ መንግሥት ፡ መመሥረት ፡ ብለን ፡ እናስበዋለን ። እስከ ፡ ፩ሺ ፡ ፱፻፲ ፡ ያለው ፡ ዘመኑ ፡ መንግሥቱ ፡ ፬፻፵፮ ፡ ዓመት ፡ ነው ።

፲፮ ፤ የፖርቱጋል ፡ መንግሥት ፡ በሺ ፡ ፩፻፴፱ ፡ ዓ. ም. ተመሠረተ ። ነገር ፡ ግን ፡ እስከ ፡ ሺ፮፻፬ ፡ ከእስጴን ፡ ነጻነቱን ፡ አላገኘም ። ከዚህ ፡ ጊዜ ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ፩ሺ ፡ ፱፻፳ ፡ ድረስ ፡ በመኻከል ፡ ፪፻፸፮ ፡ ዓመት ፡ ነው ።

፲፯ ፤ እንደምታውቁት ፡ ሻርለማ ፡ የፈረንሳይ ፡ ንጉሥ ፡ ነበር ። ከጀርመን ፡ አገር ፡ የሚበልጠውን ፡ አገር ፡ ክፍል ፡ አሸንፎ ፡ ይዞት ፡ ነበረና ፡ በ፰፻፪ ፡ ዓ. ም. መናሪያውን ፡ በዚያው ፡ አደረገ ። ግን ፡ ከንራድ ፡ የተባለ ፡ የፍራንኮኒያ ፡ ዱክ ፡ ለንጉሥነት ፡ በ፲፻፲፩ ፡ ተመረጠ ። የጀርመን ፡ መንግሥት ፡ የተጀመረበት ፡ የሚታሰበው ፡ ከዚህ ፡ ነው ። እስከ ፡ ሺ፰፻፮ ፡ ጸንቶ ፡ ቈየ ። ዘመኑ ፡ መንግሥቱ ፡ ፰፻፺፬ ፡ ዓመት ፡ ነው ።

፲፰ ፤ ኦስትሪያ ፡ እንደነገርኋችሁ ፡ ከጀርመን ፡ መንግሥታት ፡ አንዱ ፡ ነው ። አርቺዱክ ፡ ይባላል ። በሺ ፡ ፪፻፸፫ ፡ ዓ. ም. ሮዶልፍ ፡ የሀፍስቡርግ ፡ አርቺዱክ ፡ ሆነና ፡ የጀርመን ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ተባለ ። ከዚህ ፡ ዘመን ፡ ጀምሮ ፡ አውስትሪያ ፡ በኀይል ፡ እየበረታ ፡ ሄደ ። ኀይሉን ፡ የመሠረተበትና ፡ ያጸናበት ፡ ከዚህ ፡ ቀን ፡ ይጀምራል ፡ እንላለን ። ከዚህ ፡ ቀን ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ፩ሺ ፡ ፱፻ ፡ ድረስ ፡ ያለው ፡ ዘመን ፡ ፮፻፳ ፡ ዓመት ፡ መሆኑ ፡ ነው ።

፲፱ ፤ የፕረዢያ ፡ መንግሥት ፡ በሺ ፡ ፯፻፩ ፡ ተመሠረተ ። ፖላንድ ፤ አርቺዱክ ፡ ከሆነ ፡ አያል ፡ ዓመት ፡ ሆኖታል ። በ፲፻፶፱ ፡ ዓ. ም. ከቦሌስሎስ ፡ በታች ፡ ሆኖ ፡ በንጉሥ ፡ የሚገዛ ፡ ሆኖአል ። በሺ ፡ ፯፻፺፭ ፡ ረሺያ ፤ ፕረዢያ ፤ ኦስትሪያ ፡ ሁነው ፡ ያዙት ። የ፯፻፺፮ ፡ ዓመት ፡ መንግሥት ፡ ሆኖ ፡ ተቈየ ፡ ወዲህ ፡ በኋላ ፡ በመጨረሻው ፡ ከነጻነት ፡ መዝገብ ፡ ሠረዙት ፡ (ፋቁት ። )

፳ ፤ ረሺያ ፡ ቀድሞ ፡ ሳርማቲያ ፡ ይባል ፡ ነበር ። ሲቲያን ፡ የተባሉ ፡ ታርታሮች ፡ ይኖሩበታል ። በዘጠነኛው ፡ መቶ ፡ ዓመት ፡ እስካንዳኒቢያን ፡ የተባሉ ፡ ነገድ ፡ አሸነፉትና ፡ አገሩን ፡ ለጊዜው ፡ ግዛታቸው ፡ አደረጉት ። ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ደም ፡ ተፋሰሱ ። ብዙ ፡ ድካም ፡ ሆነ ። ወዲያው ፡ አገሩ ፡ ለታርታሮች ፡ ተገዛ ። ግዛታቸው ፡ እስከ ፡ ሁለትና ፡ ሦስት ፡ መቶ ፡ ዓመት ፡ ቈየላቸው ።

፳፩ ፤ ጆን ፡ ባሲሎዊትስ ፡ ፩ኛ ፡ የተባለ ፡ በሺ ፡ ፬፻፺ ፡ ከዚህ ፡ ከሚያስቅቅ ፡ ቀንበር ፡ አወጣቸው ። እንደዚህ ፡ ሆኖ ፡ ነጻነታቸው ፡ ጸናላቸው ። ከዚህ ፡ ቀን ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ፩ሺ ፡ ፰፻፹ ፡ ድረስ ፡ ያለው ፡ ዘመን ፡ ፬፻፴ ፡ ዓመት ፡ መሆኑ ፡ ነው ።

፳፪ ፤ የስዌድን ፡ መንግሥት ፡ የጥንት ፡ መንግሥት ፡ ተብሎ ፡ ይታሰባል ። በ፬፻፺፩ ፡ ፈራጆች ፡ የነበሩት ፡ የንጉሥነትን ፡ ማዕርግ ፡ ወሰዱ ። የነርሱም ፡ ዘር ፡ እስከ ፡ ሺ፰፰ ፡ ገዙ ። በዚያ ፡ ዘመን ፡ ስዌድን ፡ ሰፊ ፡ አገር ፡ አልነበረም ። ሕዝቡም ፡

እንደ ፡ አራዊት ፡ ነበሩ ። መንግሥቱም ፡ ገና ፡ ያልተረጋጋ ፡ መንግሥት ፡ ነበር ። በ፱፻፺፩ ፡ አሎፍ የተባለ ፡ ንጉሣቸው ፡ የክርስቲያንን ፡ ሃይማኖት ፡ ተቀበለና ፡ አገ ሩንም ፡ ሥርዓት ፡ ያለው ፡ መንግሥት ፡ አደረገው ። ከዚህ ፡ ቀን ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ፩ሺ፡፰፻፹ ድረስ ፡ የነበረው ፡ ዘመን ፡ ፰፻፹፯ ፡ ዓመት ፡ ነው ።

፳፱ ፤ መጀመርያ ፤ የዳንማርክ ፡ ንጉሥ ፡ እስክዮልድ ፡ ነበር ፡ ይባላል ፤ ጎርም ፡ ሽማግሌው ፡ የተባለ ፡ የተበታተኑትን ፡ አያሎች ፡ የሚሆኑ ፡ ነገደ ፡ ደንማርክን ፡ ባንድነት ፡ ሰብስቦ ፡ አንድ ፡ መንግሥት ፡ አድርጎ ፡ እስኪገለጥ ፡ እርሱንም ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ ወራሾቹን ፡ እስከ ፡ ፱፻፳ ፡ ዓመት ፡ የምናውቀው ፡ ጥቂት ፡ ነው ። ከዚህ ፡ ቀን ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ፲፰፻፹ ፡ ድረስ ፡ ፱፻፷ ፡ ዓመት ፡ ነው ።

፴ ፤ ሆላንድን ፡ ጥንት ፡ ቤልጅጎች ፡ ይዘውት ፡ ነበር ። ቀድሞ ፡ በ፰፻፷፰ ፡ ዓ. ም ካውንት ፡ ቴሪ ፡ የተባለ ፡ መንግሥት ፡ አቆሙ ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ የቡርጉንዲ ፡ ዱክ ፡ ያዘው ። ቀጥሎ ፡ በእስጳንያ ፡ ንጉሥ ፡ እጅ ፡ ወደቀ ። በሺ፡፭፻፹፩፡ዓ. ም. ሕዝቡ ፡ ዐመፁና ፡ ለራሳቸው ፡ ሬፑብሊክ ፡ አቆሙ ።

፴፩ ፤ ሆላንድ ፡ በራሱ ፡ አዳሪ ፡ ሆኖ ፡ ነጻ ፡ ያገኘበትን ፡ ከዚህ ፡ እንጀምራለን ። ቤልጊ ሺ፰፻፲፬ ፡ እስኪሆን ፡ ገና ፡ መንግሥት ፡ ተብሎ ፡ አልተቋቋመም ፡ ነበር ። ቤልጊ ውም ፡ ጥንት ፡ ከሆላንድ ፡ ጋር ፡ የተደረበ ፡ ነበር ። የኔድርላንድ ፡ መንግሥት ፡ ተብሎ ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ አቆመና ፡ በሺ፡፰፻፴፡ራሱን ፡ የቻለ ፡ ነጻ ፡ ያለው ፡ መን ግሥት ፡ ሆነ ።

፴፪ ፤ ስዊትዝርላንድ ፡ ለሮማውያን ፡ ከተገዛ ፡ በኋላ ፡ በሺ፡፫፻፲፭ ፡ ፈረንሳይና ፡ ጀር መን ፡ ነጻነት ፡ ያላቸው ፡ ሕዝብ ፡ ሆኑ ። ከዚህ ፡ ቀን ፡ ጀምሮ ፡ እስከ፡፩ሺ፡፰፻፹ ፡ ድረስ ፡ ያለው ፡ ዘመን ፡ ፭፻፷፭ ፡ዓመት ፡ ነው ።

፴፫ ፤ የመጀመርያው ፡ የናፕል ፡ ገዢ ፡ የንጉሥን ፡ ማዕርግ ፡ የወሰደ ፡ ሮጂር ፡ የተ ባለ ፡ በሺ፡፻፴፡ዓ. ም. ነገሠ ። ሰርዲኒያን ፡ በሺ፡፫፻፫ ዓ. ም. እስጳኞች ፡ ወሰ ዱትና ፡ እስከ ፡ ሺ፯፻፰ ፡ ድረስ ፡ ከእጃቸው ፡ አልወጣም ። በኋላ ፡ እንግሊዞች ፡ ወስደው ፡ ለሳቮይ ፡ ዱክ ፡ ሰጡት ። ይህም ፡ የሳቮይ ፡ ዱክ ፡ በሺ፡፯፻፳፡የንጉሥን ፡ ማዕርግ ፡ ያዘ ። ጄኔዋ ፤ ፒድሞንት ፤ ሳቮይ ፤ ወደ ፡ መንግሥት ፡ ተጨመሩ ። አሁንም ፡ የኢጣሊያ ፡ መንግሥት ፡ ክፍል ፡ ናቸው ።

፴፬ ፤ ቬኒስ ፡ በ፮፻፺፯ ፡ ሬፑብሊክ ፡ ሆነ ። ፖዎሊቺ ፤ አናፌስቶ ፤ ሳቮይ ፡ መጀ መርያ ፡ ዳኞች ፡ ነበሩ ። በሺ ፡ ፯፻፺፯ ፡ ናፖሊዮን ፡ እስኪይዘው ፡ ኀይለኛ ፡ መን ግሥት ሆኖ ፡ በነጻነት ፡ ቈየ ። በኋላም ፡ ወደ ፡ አውስትሪያ ፡ ተጨመረ ። አሁን ግን ፡ የኢጣሊያ ፡ ክፍል ፡ ሆኖአል ።

## ጥያቄ ።

፩ ፤ ኬልቶች ፡ እንዴት ፡ ሆኑ ፡ ? ወደ ፡ ኤውሮጳ ፡ እንደምን ፡ አድርገው ፡ ገቡ ፡ ?

፪ ፤ እንደ ፡ እውነት ፡ የሚባለው ፡ እንዴት ፡ ነው ፡ ? እርግጡ እንዴት ፡ ይገ ለጻል ፡ ?

፫ ፤ በኤውሮጳ ፡ ቀድሞ ፡ ሰው ፡ የገባው ፡ በየት ፡ በኩል ፡ ነው ፡ ?

፬ ፤ አቴን ፡ ምን ፡ ጊዜ ፡ ተመሠረተ ፡ ? የቈረቈረውስ ፡ ? የመሠረተውስ ፡ ማነው ፡ ?
የግሪኮች ፡ ታሪክ ፡ ምን ፡ ጊዜ ፡ ይጀመራል ፡ ?

፭ ፤ የግሪክ ፡ ነጻነት ፡ የተወሰነው ፡ ምን ፡ ጊዜ ፡ ነው ፡ ?
ምን ፡ ያህል ፡ ጊዜ ፡ ጸንቶለት ፡ ኖረ ፡ ?

፮ ፡ ስለ ፡ ሮም ፡ ምን ፡ ትላላችሁ ፡ ? መንግሥቱ ፡ ምን ፡ ያህል ፡ ጊዜ ፡ ጸንቶለት ፡ ኖረ ፡ ?

፯ ፤ የግሪክ ፡ መንግሥት ፡ እንዴት ፡ ሆነ ፡ ? ምን ፡ ጊዜ ፡ ተጀመረ ፡ ?

፰ ፤ እንደምን ፡ አድርጎ ፡ ተወስኖ ፡ ነበር ፡ ?

፱ ፤ ቱርክ ፡ እንዴት ፡ ነበር ፡ ? የቱርክ ፡ ግዛት ፡ ስፋት ፡ እስከየት ፡ ይደርሳል ፡ ?

፲ ፤ የኦቶማንን ፡ መንግሥት ፡ የመሠረተ ፡ ማነው ፡ ? የኦቶማን ፡ መንግሥት ፡ ምን ፡ ያህል ፡ ጊዜ ፡ ኖረ ፡ ?
ቊስጥንጥንያ ፡ እንደምን ፡ ሆነ ፡ ?

፲፩ ፤ ቼልዱሪክ ፡ እንዴት ፡ ሆነ ፡ ? ክሎቪስስ ፡ ? የፈረንሳይ ፡ ሞናርኪ ፡ በንጉሥ ፡ ብቻ ፡ አገዛዝ ፡ ስንት ፡ ያህል ፡ ኖረ ፡ ?

፲፪ ፤ ኤግበርት ፡ እንዴት ፡ ያለ ፡ ነው ፡ ? የእንግሊዝ ፡ ሞናርኪ ፡ በንጉሥ ፡ ብቻ ፡ አገዛዝ ፡ ምን ፡ ያህል ፡ ቈየ ፡ ?

፲፫ ፤ (ሙርስ) ፡ ሞርኮች ፡ እንደምን ፡ ሆኑ ፡ ? ፒላጂዎና ፡ ወራሹ ፡ ምን ፡ አደረገ ፡ ?

፲፬ ፤ ፌርዲናንድ ፡ እንዴት ፡ ሆነ ፡ ? ካስቲልና ፡ አራጎን ፡ በምን ፡ ተባበሩ ፡ ?
የእስጳንያ ፡ መንግሥት ፡ ሥርዓት ፡ የጀመርው ፡ ምን ፡ ጊዜ ፡ ነው ፡ ? ምን ፡ ያህል ፡ ቈየ ፡ ?

፲፭ ፤ የፖርቱጋል ፡ መንግሥት ፡ እንደምን ፡ ሆነ ፡ ?

፲፮ ፤ ሻርለማኝ ፡ እንዴት ፡ አደረገ ፡ ? ኮንራድስ ፡ ?
የጀርመን ፡ መንግሥት ፡ ምን ፡ ያህል ፡ ጊዜ ፡ ኖረ ፡ ?

፲፯ ፤ የኦስትሪያ ፡ አርቺዱክ ፡ እንደምን ፡ ሆነ ፡ ? ምን ፡ ያህል ፡ ጊዜ ፡ ኖረ ፡ ?

፲፰ ፤ ፕሩሲያ ፡ ምን ፡ ያህል ፡ ጊዜ ፡ ቈየ ፡ ?

፲፱ ፤ ረሺያ ፡

፳ ፤ እንደምን ፡ ነጻነት ፡ አገኘ ፡ ? ምን ፡ ያህል ፡ ጊዜ ፡ ኖረ ፡ ?

፳፩ ፤ የስዊድን ፡ መንግሥት ፡ ስንት ፡ ያህል ፡ ጊዜ ፡ ቈይቶአል ፡ ?

፳፪ ፤ ደንማርክ ፡ ምን ፡ ያህል ፡ ጊዜ ፡ ኖረ ፡ ?

፳፫-፳፬ ፤ ሆላንድ ፡ መንግሥት ፡ የሆነው ፡ ምን ፡ ጊዜ ፡ ነው ፡ ?

፳፭ ፤ ስዊትዝርላንድ ፡ ምን ፡ ያህል ፡ ጊዜ ፡ ኖረ ፡ ?

፳፮ ፤ ናፕልስ ፡ ? ሳርዲያን ፡ ? ጄኒዋ ፡ ? ፒዬድሞንት ፡ ? ሳቮይ ፡ ?

፳፯ ፤ ቬኒስ ፡ የማን ፡ ገንዘብ ፡ ሆነ ፡ ?

## ምዕራፍ፡ ፪፻፲፡ እንደ፡ ገና፡ ምርምር።

### የአገሮች፡ ጥንታዊ፡ ስም።

፩፡ በኤውሮጳ፤ በእስያ፤ በአፍሪካም፤ አያሎች፡ አገሮች፡ ጥንት፡ ይጠሩበት፡ የነበረ፡ ስማቸው፡ ቀርቶ፡ አሁን፡ በሌላ፡ ስም፡ ይጠራሉ። ስለዚህ፡ በነዚህ፡ በሦስቱ፡ ዓለማት፡ የሚገኙትን፡ መንግሥታት፡ የጥንቱንና፡ የዛሬውን፡ ስማቸውን፡ እየለየሁ፡ ሕዝባቸውም፡ ከማን፡ ነገድ፡ የወጡ፡ መሆናቸውን፡ እንደሚቻል፡ አድርጌ፡ እገልጽላችኋለሁ።

### እስያ።

| የዛሬው፡ ስማቸው። | የጥንት፡ ስማቸው። | የጥንቱ፡ ባላገሮች። | የዛሬው፡ ነገዶች፡ የማን፡ ዘሮች፡ እንደሆኑ። |
|---|---|---|---|
| ናቶሊያ፡ | እስያሚኖር፡ | ነገደ፡ ያፌት፡ | የጥንቱ፡ ባላገሮች፡ |
| ፐለስታይን፡ | ከነአን፡ | ነገደ፡ ሴም፡ | ግሪኮች፤ አይሁድ፤ ቱርኮች፡ |
| » » » | » » | » » | ሌሎችም፡ |
| » » » | » » | » » | የጥንቱ፡ ባላገሮች፡ አይሁዶች፡ ቱርኮች፡ |
| (ሴሪያ)፡ ሶርያ፡ | (ሴሪያ)፡ ሶርያ፡ | | ጥንት፡ ከሌሎች፡ ጋር፡ የነበሩ። |
| አርሚኒያ፡ | አርማኒያ፡ | | |
| ዲያርቤኪር፡ | ሚሶጶታሚያ፡ | | |
| ጉርዲስታን፡ | (አሲሪያ፡) አሶር፡ | | |
| ባግዳድ፡ | ባቢሎናውያን፡ ከለዳውያን፡ | | |
| አዲርቤቲዛን፡ | ሚዶን፡ | | |
| ኢራክ፡ አጀሚ፡ | ፓርቲያ፡ | | |
| ኮራዛን፡ | ሄርካኒያ፡ | | |
| ፔርሲያ፡ | ፔርስያ። (ፋርስ፡) | | ነገደ፡ ኤላም። |
| አስትራካን፡ | አሲያቲክ፤ ሳርማቲያ፡ | | ነገደ፡ ሴም። |
| ካቡሊስታን፡ | ባክትሪያ፡ | | |
| ሲቢሪያ፤ ታርታሪ፡ | ሲቲያ። | | |

## አፍሪካ።

| የዛሬው፡ ስም። | የጥንቱ፡ ስም። | የጥንት፡ ነገድ። | የዛሬው፡ ነገድ። |
|---|---|---|---|
| ኢጂብት፡ (ግብፅ፡) | ኢጂብት፡ | ነገደ፡ ካም። | ከጥንት፡ ዘራቸው፡ ከቱርክና፡ ከሌሎችም፡ የተቀላቀሉ፡ ናቸው። |
| ትሪፖሊ፤ | የቱኒስ፡ክፍል፡ አፍሪካ፡ | ግሪኮች፡ካርታጐች፡ | ከጥንት፡ ዘራቸው፡ ዐረቦችና ቱርኮች፡ ናቸው። |
| ሞርኮ፡ ቤሌዱልጂሪዳ፡ ኑቢያና፤ አቢሲኒያ። | ሞሪታኒያ፤ ጂቱሊያ፤ ኢትዮጵያ። | ሞሪ፡ወይም፡ሙሮች ጁቲሊ። | የጥንት፡ ባላገሮች። |

## ኤውሮጳ።

| የዛሬው፡ ስም። | የጥንቱ፡ ስም። | የጥንት፡ ነገድ። | የዛሬው፡ ነገድ። |
|---|---|---|---|
| ኖርዌ፡ ስዌድን፤ ደንማርክ፤ | እስካንዲናቪያ፤ | ነገደ፡ጐት፡እስካንዲ፡ ናቪያን፡ ይባላሉ። | |
| ጁትላንድ፤ | ሲምቢሪያ፤ | ሲምሪ። | |
| ረሺያ፤ | ሳርማቲያ፤ | ታርታሮች፤ | ታርታሮች፡ እስካንዲናቪያን፡ ሌሎችም፡ ነገዶች። |
| ታላቅ፡ ብሪቴን፤ | ብሪታንያ፤ | ኬልቶች፡ጌልስ፤ | ሳክሶን፡ ዲንስ፡ ብሪትንስ። |
| እስኮትላድ፤ | ካሌዶኒያ፤ | ኃይላንድስ፡ኬልትስ፡ ሎላንድ፡ፒክትስ፡ | ኖርማን፡ፍሬንች፡ |
| አየርላድ፤ | ሄቤርኒያ፤ | ኬልቶች፡ ወይም፡ ጎሎች፡ | የቀድሞ፡ ወገኖች፡ ናቸው። |
| ሆላንድና፡ ቤልጊውም፡ | ቤልጂካ፤ | ቤልጂ። | |
| ፈረንሳይ፤ | ጎሎች፤ | ኬልት፡ ጎል፤ | ኬልትስ፡ ፍራንክስ፡ ኖርማን። |
| ጀርመን፤ | ጀርማኒያ፤ | ቱውቶኒክ፡ አልማኚ፡ ሌላም፡ ነገድ። | የጥንት፡ነገድ፡ናቸው |
| ስዊትዝርላንድ፤ ቲሮል፤ ሮማኒያ፤ | ሄልዌትያ፤ ሬቲያ። ትሬስ። | ሄልቬቲ። | |

| | | | |
|---|---|---|---|
| እስጴን ፤ | ሂስጳኒያ ፤ | ካርታጎች ፤ ግሪኮች ፤ | ዘራቸው ፡ ጎቶች ፤ ዋን ፡ ዳልዎች ፤ ሌሎ ችም ፡ ናቸው ። |
| ፖርቱጋል ፤ | ሉሲታኒያ ፡ | | |
| ሳቮይ ፤ ፔድሞት ፤ | ሲሳልፒን ፤ ጎል ፤ | ኬልት ፤ | ነገደ ፡ ጎት ። |
| መቄዶንያ ፤ | መቄዶንያ ፤ | | |
| ግሪክ ፡ | ግሪክ ፤ | ፈኒቂያን ፡ ኢጂብቲ ያን ፡ | የጥንት ፡ ወገኖች ። |

## ምዕራፍ ፡ ፪፻፲፩ ፡ ዋና ፡ የሚታይ ።

### የመንግሥት ፡ መሠረትና ፡ ፀዕውቀት ፡ ከፍ ፡ እያለ ፡ መሄድ ።

፩ ፡ አሁን ፡ አንባቢዬ ፡ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ የደከመ ፡ ይመስላል ። ዳሩ ፡ ግን ፡ ስለ ፡ እያሎች ፡ ዋና ፡ ዋና ፡ ነገሮች ፡ ባጭሩ ፡ እስክናገር ፡ ድረስ ፡ ጥቂት ፡ እንዲታገሠኝ ፡ እለምናለሁ ። መጀመርያ ፡ ስለ ፡ መንግሥት ፡ አገዛዝ ፡ እናገራለሁ ።

፪ ፡ ልብ ፡ ታደረጉ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ አሁን ፡ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ አንድ ፡ አንዱ ፡ ነገድ ፡ ወይም ፡ ሕዝብ ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ መንገድ ፡ ይገዛል ። ሌላውም ፡ በሌላ ፡ መንገድ ፡ ይገዛል ። ባሜሪካ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ሕዝቡ ፡ በመረጡአቸው ፡ ገዥችና ፡ ሕዝቡ ፡ ራሳቸው ፡ በወጡት ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ ይገዛሉ ። ስለዚህ ፡ ሕዝቡ ፡ ሬፑብሊክ ፡ ይባላሉ ።

፫ ፡ አንዳንዱ ፡ ሕዝብ ፡ እንደ ፡ ፈቃዳቸው ፡ በሚገዙዋቸው ፡ በነገሥታት ፡ ወይም ፡ በቄሣሮች ፡ ይገዛሉ ። እነዚህም ፡ ባለሙሉ ፡ ሥልጣን ፡ ሁነው ፡ በራሳቸው ፡ ሥልጣን ፡ እንደ ፡ ፈቃዳቸው ፡ የሚገዙ ፡ ናቸው ። ሌሎቹ ፡ ሕዝብ ፡ ደግሞ ፡ ሥልጣናቸው ፡ በሕዝብ ፡ በተወሰነ ፡ ነገሥታትና ፡ ቄሣሮች ፡ ይገዛሉ ።

፬ ፡ ዓለም ፡ ሁልጊዜ ፡ እንዲህ ፡ እንደ ፡ አሁኑ ፡ ሁኔታ ፡ እየሆነ ፡ የተገዛ ፡ አይምሰላችሁ ። የመጀመርያው ፡ አገዛዝ ፡ የተነሣው ፡ አባት ፡ በቤተ ፡ ሰቡ ፡ ላይ ፡ እንዴት ፡ እንደሚገዛ ፡ በመመልከት ፡ ነው ። የመጀመርያ ፡ አገዛዝ ፡ ዐይነት ፡ አባት ፡ በልጆቹ ፡ ላይ ፡ ይገዛል ። እንዲታዘዙት ፡ ይፈልጋል ። ቀጥለውም ፡ የልጅ ፡ ልጆቹ ፡ ሁሉ ፡ የወላጆቻቸውን ፡ ምሳሌ ፡ ይከተላሉ ። በዚሁ ፡ ምሳሌ ፡ መላው ፡ ቤተ ሰብ ፡ ለወላጆቻቸው ፡ ይታዘዛሉ ።

፭ ፡ ይህም ፡ ዐይነት ፡ አገዛዝ ፡ ያባቶች ፡ አገዛዝ ፡ ይባላል ። ይህም ፡ ዐይነት ፡ አገዛዝ ፡ ከጥፋት ፡ ውሃ ፡ በፊት ፡ ይኖር ፡ የነበረው ፡ አገዛዝ ፡ ነው ።
ከዚያም ፡ ወዲህ ፡ ይህ ፡ ዐይነት ፡ በእስያ ፡ በብዙ ፡ ስፍራ ፡ አሸንፎ ፡ ኖረ ። ከዚያ ፡ ወዲህ ፡ የሰው ፡ ነገድ ፡ በብዙ ፡ ተከፋፍሎ ፡ ነበር ። እነዚህም ፡ እርስ ፡ በርሳቸው ፡ እየተዋጉ ፡ ተጠቃለሉ ። በሚከተለው ፡ ትግል ፡ ጥቂት ፡ ሰዎች ፤ ከፍተኛነትንና ፡ ኀይልን ፤ ብርታትንና ፡ ብልሀትንም ፡ አሳዩ ። እነዚህም ፡ መሪዎች ፡ ሆኑ ። ታላቅም ፡ ሥልጣን ፡ አገኙ ።

፮ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ሥልጣን ፡ ማግኘት ፡ ይወዳል ። እነዚህም ፡ በሕዝብ ፡ ላይ ፡ መግዛትን ፡ አገኙ ። ይህ ፡ ሁሉ ፡ ሁለተኛውን ፡ አገዛዝ ፡ አስገኘ ፤ መሪውም ፡ አለቃ ፡ ሆነ ፤ መቼውንም ፡ ጦረኛው ፡ ነገድ ፡ ከአውሬነቱ ፡ ይነሣና ፡ ጨካኝ ፡ መንግሥት ፡ ይሆናል ።

፯ ፡ ሕዝብ ፡ ከፍ ፡ ብሎ ፡ እየአበረ ፡ መንደሮችና ፡ ከተሞችን ፡ በሠራ ፡ ጊዜ ፡ የወታደር ፡ መሪ ፡ የሆነው ፡ ለሕዝቡ ፡ የማይስማማ ፡ ደስታ ፡ የማያመጣላቸው ፡ ይሆናል ። ስለዚህ ፡ ሕዝቡ ፡ ከታላቅ ፡ ማዕርግ ፡ ጋር ፡ ድምፃቸው ፡ የሚሰማ ፡

ገዦች ፣ ይመኛሉ ። ለነዚህም ፣ በሠራዊት ፣ ታጅቦ ፣ ታላቅ ፣ መታየትና ፣ ሥር
ዓተ ፣ ንግሥም ፣ አስፈላጋቸው ። በራሳቸው ፣ ዘውድ ፣ ይደፋሉ ። ቤተ ፣ መንግ
ሥቶች ፣ አሠርተው ፣ በዚያ ፣ ይኖራሉ ።

፰ ፤ ለንጉሥ ፣ የሚገባውን ፣ ከበሬታ ፣ ለማግኘት ፣ የከበረ ፣ ልብስ ፣ በለበሱ ፣ ሰዎች
ይታጀባሉ ። የንጉሥነት ፣ አካሄድና ፣ ልዕልና ፣ ለማሳየት ፣ ከሕዝብ ፣ በላይ ፣ የሚ
ሆን ፣ ከፍ ፣ ያለ ፣ ደረጃ ፣ ያሳያሉ ። ይህም ፣ ሦስተኛው ፣ ዐይነት ፣ የመንግ
ሥት ፣ አገዛዝ ፣ ነው ። የንጉሥ ፣ አገዛዝ ፣ ይባላል ።

፱ ፤ ነገሥታትና ፣ ገዦች ፣ ሕዝቡን ፣ እንደባርያ ፣ በማድረጋቸው ፣ ራሳቸውን ፣
ወዳጆች ፣ መሆናቸው ፣ ስለ ፣ ታወቀ ፣ ባንዳንድ ፣ አገር ፣ ሕዝቡ ፣ ገዦቻችውን ፣
ይመርጣሉ ። ለራሳቸውም ፣ ሕግ ፣ ያወጣሉ ። ይህም ፣ አራተኛው ፣ ዐይነት ፣ የመንግ
ሥት ፣ አገዛዝ ፣ ነው ። ይህም ፣ ሬፑብሊክ ፣ ይባላል ።

፲ ፤ የመጀመርያው ፣ ዐይነት ፣ አገዛዝ ፣ ያባቶች ፣ አገዛዝ ፣ መባሉን ፣ ልብ ፣ አድርጉ ።
ይህንንም ፣ ሕዝቡ ፣ ጥንት ፣ ዘመን ፣ ያደርጉት ፣ የነበረው ፣ ነው ። ይህም ፣ በተደረገ ፣
ጊዜ ፣ ከሕዝቡ ፣ የሚበዙት ፣ ሥራቸው ፣ እርሻና ፣ ከብት ፣ ማርባት ፣ ነበር ። ሁለተኛው
ዐይነት ፣ አገዛዝ ፣ በላይ ፣ የሚሆን ፣ አንድ ፣ አለቃ ፣ ይመርጣሉ ። ይህም ፣ ዐይነት ፣ አገዛዝ ፣
ጦረኞች ፣ የሆኑ ፣ ነገድና ፣ ገና ፣ ወደ ፣ ሥልጣኔ ፣ ያልደረሱ ፣ ሰዎች ፣ የሚያደርጉት ፣ ነው ።

፲፩ ፤ ሦስተኛው ፣ ዐይነት ፣ አገዛዝ ፣ ሕዝብ ፣ ከፍ ፣ ወደ ፣ አለው ፣ ሥልጣኔ ፣ ከደረሱ ፣
በላይ ፣ የሚያደርጉት ፣ ነው ። ይህም ፣ የጥንት ፣ የአሦራውያንና ፣ የፋርሶች ፣ አገዛዝ ፣
ነበር ። ከዚያን ፣ ዘመን ፣ ጀምሮ ፣ ይህ ፣ ዐይነት ፣ አገዛዝ ፣ ከሌላው ፣ ዐይነት ፣ ይልቅ ፣
በሰው ፣ ወገን ፣ ሁሉ ፣ እጅግ ፣ ኀይለኛ ፣ ሆኖ ፣ ኖረ ። እሁን ፣ ያለው ፣ ሕዝብ ፣ ከሥሩ ፣
ዘጠኝ ፣ እጅ ፣ ለንጉሥ ፣ መንግሥት ፣ ይገዛል ።

፲፪ ፤ የሬፑብሊክን ፣ አገዛዝ ፣ አይሁድ ፣ ከግብፅ ፣ እንደ ፣ ተመለሱ ፣ ተቀብለውታል ፣ ነገር ፣
ግን ፣ የሬፑብሊክ ፣ አገዛዝ ፣ እስከ ፣ ግሪኮች ፣ ዘመን ፣ አልቈየም ። አያሌዎች ፣ የግሪክ ፣ መን
ግሥታት ፣ በልዩ ፣ ልዩ ፣ ዘመን ፣ እነርሱው ፣ ራሳቸውን ፣ የሬፑብሊክን ፣ አገዛዝ ፣
አቆሙ ። ዳሩ ፣ ግን ፣ ይህም ፣ ቢሆን ፣ ለጥቂት ፣ ጊዜ ፣ ብቻ ፣ ሆነና ፣ ራሳቸውን ፣
እንደ ፣ ነገሥታት ፣ ያደረጉ ፣ ሰዎች ፣ ገለበጡት ።

፲፫ ፤ ሮም ፣ አንድ ፣ ጊዜ ፣ ሬፑብሊክ ፣ ሆኖ ፣ ነበር ። ወዲያው ፣ በንጉሥ ፣ ሥል
ጣን ፣ ብቻ ፣ የሚገዛ ፣ ሆነ ። ሌሎቹ ፣ አገሮች ፣ ግን ፣ ሬፑብሊክ ፣ ተባሉ ፣ ለባላ
ገሮቹ ፣ ሁሉ ፣ ነጻነት ፣ ያለው ፣ ታሁን ፣ ቀደም ፣ ዋና ፣ ሆኖ ፣ የታየው ፣ የዩናይ
ትድ ፣ እስቴትስ ፣ አሜሪካ ፣ አገዛዝ ፣ ነው ። ግን ፣ በዚሁ ፣ አገር ፣ ብዙ ፣ ሚሊዮን ፣
ጥቍሮች ፣ ደስ ፣ ሳይላቸው ፣ በባርነት ፣ ይኖራሉ ።

## ጥ ያ ቄ ።

፩ ፤ አሜሪካ ፣ እንደምን ፣ አድርጎ ፣ ይገዛል ፣ ? አገዛዙ ፣ ምን ፣ ይባላል ፣ ?

፫ ፤ በገዛ ፣ ራሳቸው ፣ የሚገዙ ፣ ነገሥታት ፣ ማለት ፣ እንዴት ፣ ነው ፣ ? የተ
ወሰኑ ፣ አገዛዞች ፣ የሚባሉት ፣ እንዴት ፣ ናቸው ፣ ?

፬ ፤ ከጥንት ፡ ያገዛዝ ፡ መንገድ ፡ ከምን ፡ ተገኘ ፡?

፭ ፤ የፓትርያርክ ፡ አገዛዝ ፡ የሚሉት ፡ እንዴት ፡ ያለ ፡ ነው ፡? ጠረኞች ፡ የተባሉ ፡ ነገድ ፡ እነዜት ፡ ናቸው ፡?

፮ ፤ ሁለተኛው ፡ ዐይነት ፡ አገዛዝ ፡ ወይም ፡ መንግሥት ፡ የተባለው ፡ እንዴት ፡ ነው ፡?

፯ ፤ የሕዝብ ፡ አገዛዝ ፡ እየተሻሻለ ፡ ስለሄደ ፡ የሕዝቡ ፡ አሳብ ፡ እንዴት ፡ ነው ፡?

፰ ፤ የንጉሥ ፡ አገዛዝ ፡ ሁኔታው ፡ እንዴት ፡ ነው ፡?

፱ ፤ የሬፑብሊክ ፡ አገዛዝ ፡ ዐይነት ፡ እንዴት ፡ ነው ፡?

፲ ፤ የመጀርያው ፡ ዐይነት ፡ እንዴት ፡ ነው ፡? ሁለተኛውስ ፡ እንዴት ፡ ነው ፡?

፲፩ ፤ ሦስተኛውስ ፡ ዐይነት ፡ እንዴት ፡ ነው ፡?

፲፪ ፤ የሬፑብሊክ ፡ ወገን ፡ አገዛዝ ፡ እንዴት ፡ ነው ? የግሪኮች ፡ እንዴት ፡ ነው ፡? የሮማውያንስ ፡ ? የዩናይትድ ፡ እስቴት ስ ፡ ?

---

## ምዕራፍ ፡ ፪፻፲፪ ።

### የቤት ፡ ሥራ ፡ ዕውቀት ፤ ግበርና ፤ የአትክልት ፤ ሥራ ።

፩ ፤ መጀመርያ ፡ የሰው ፡ ማደርያ ፡ የነበረው ፡ ተፈጥሮ ፡ እንደ ፡ አመለከተው ፡ ለችግራቸው ፡ በቂ ፡ የነበረው ፡ ዋሻ ፡ ቤት ፤ ድንኳን ፡ ነበር ። ሥልጣኔ ፡ እየገፋ ፡ እየቀደመ ፡ ሲመጣ ፡ ጊዜ ፡ ጠንካራ ፡ ቤቶች ፡ መሥራትና ፡ ችጋርና ፡ ድካም ፡ የሌለው ፡ አናኑዋር ፡ መኖር ፡ ተጀመረ ። ድንጋይ ፡ ወይም ፡ ጡብ ፡ ለሥራቸው ፡ የተስማማቸው ፡ ሆነላቸው ። መጀመርያ ፡ ያለስሚንቶ ፡ በኋላ ፡ እንዴት ፡ አድርገው ፡ ለመሥራት ፡ ከተማሩ ፡ በኋላ ፡ ግን ፡ ለጣያቶቻቸው ፡ ቤተ ፡ ጣዖት ፡ ሠሩ ። ሲሠሩትም ፡ ከመኖሪያቸው ፡ የተሻለ ፡ አድርገው ፡ ሠሩት ።

፪ ፤ ጥንት ፡ መጀመርያ ፡ የተገኘው ፡ ብልሀት ፡ የቤት ፡ አሠራር ፡ ብልሀት ፡ ነው ። ሥራውም ፡ ለኋለኞቹ ፡ ትውልድ ፡ እየተወራረሰ ፡ የጥንቱን ፡ ሥራ ፡ እያስመሰሉ ፡ ይሠሩት ፡ ጀመር ። መሣሪያም ፡ ቢጕድል ፡ ስፍራና ፡ አየርም ፡ ባይመች ፡ ያንኑ ፡ እያስመሰሉ መሥራታቸው ፡ አልቀረም ።

፫ ፤ መጀመርያ ፡ ግበያች ፡ የቤት ፡ አሠራርን ፡ ብልሀት ፡ ያገኙት ፡ ከዋሻ ፡ ነው ። (ማለት ፡ ዋሻን ፡ ተመልክተው ።) ቺኖች ፡ ድንኳንን ፡ ተመልክተው ፡ ነው ። ግሪኮ ፡ ከመርከብ ፡ ክፍል ፤ ጎቶች ፡ ከዛፍ ፡ ጥላ ፡ ነው ። ቤት ፡ መሥራት ፡ እያደር ፡ ዋና ፡ ብልሀት ፡ ሆነና ፡ ቤተ ፡ መንግሥትንና ፡ ቤተ ፡ መቅደሶችን ፡ መሥራት ፡ ባጣም ፡ የማያደክም ፡ ነገር ፡ ሆነ ። የዐምድ ፡ አቋቋም ፡ መደርደር ፤ የቅስት ፡ ሥራ ፡ ያደባባይ ፡ ሁኔታ ፡ ይህ ፡ ሁሉ ፡ ተገለጠ ። ግንዱ ፡ እየታነጠ ፡ ምሰሶ ፡ ይሆን ፡ ጀመር ። ከተፈጥሮው ፡ ዋሻ ፡ የነበረውን ፡ ያማረ ፡ መቅደስ ፡ አድርገው ፡ ይሠሩት ፡ ጀመር ።

፬ ፤ መጀመርያ ፡ ቤት ፡ ስለ ፡ መሥራት ፡ ያሰቡ ፡ የቤሉስን ፡ መቅደስ ፡ የሠሩና ፡ ያትክልትን ፡ ሥራ ፡ የተጠበቡ ፡ ባቢሎናውያን ፡ ናቸው ። አሦራውያንም ፡ የሚታየውን ፡ ሕንፃ ፡ በነነዌ ፡ በብዙ ሠርተዋል ። ፊኒቅያዎችም ፡ ከተሞቻቸውን ፡ እጅግ ፡ አስጊጠዋቸዋል ። የእስራኤላውያንም ፡ ቤተ ፡ መቅደስ ፡ ሥራው ፡ እጅግ ፡ አድርጎ ፡ የሚያስደንቅ ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ ይታሰባል ። ስለ ፡ ፋርሶችና ፡ ስለ ፡ ግብፃውያን ፡ ሕንፃዎች ፡ የሆኑ ፡ እንደ ፡ ሆን የጥንት ፡ ፍራሾች ፡ ቅሬታ ፡ እስካሁን ፡ አሉን ፤ እጅግ ፡ ከፍታ ፡ ያላቸው ፡ ናቸው ።

፭ ፤ የግሪኮች ፡ ሥራ ፡ መጀመርያ ፡ ታይቷል ። እጅግ ፡ ቀላል ፡ ነው ። የቤቱን ፡ ሕንፃ ፡ መልክ ፡ ዶሪክ ፡ አሠራር ፡ ይሉታል ። በኋላ ፡ በዚሁ ፡ በዶሪክ ፡ አሠራር ፡ ላይ ፡ የአዮኒክና ፡ ፡ ቆሮንቶስ ፡ ሰዎች ፡ ሥራ ፡ ዐይነት ፡ እየተጨመረ ፡ ይሠራ ፡ ጀመር ። ከዖሎፖኒሲያን ፡ ጦርነት ፡ በኋላ ፡ ይህ ፡ ቀላሉ ፡ ሥራ ፡ እየቀረ ፡ ሌላ ፡ የጌጥ ፡ ዐይነት ፡ እየተጨመረ ፡ ይሠራ ፡ ጀመር ። በ፫፻፴፫ ፡ ተክርስቶስ ፡ ልደት ፡ በፊት ፡ እስክንድር ከሞተ ፡ በኋላ ፡ የብልሀት ፡ ሥራ ፡ እያነሰ ፡ ሄደና ፡ በግሪክ ፡ አገር ፡ ብቻ ፡ ጥቂት ፡ ይሠራ ፡ ነበር ።

፮ ፤ ሮማውያንም ፡ ይሠሩ ፡ ነበር ። ዳሩ ፡ ግን ፡ እስከ ፡ አውግስጦስ ፡ ዘመን ፡ ድረስ ፡ እንደ ፡ ግሪኮች ፡ አድርገው ፡ ለመሥራት ፡ አልቻሉም ። አውግስጦስ ፡ የግሪኮችን ፡ አናጢዎች ፡ በሮም ፡ ያማረ ፡ ሕንፃ ፡ እንዲሠሩ ፡ ያበራታቸው ፡ የነበረ ፡ ነው ። ነገር ፡ ግን ፡ ዋና ፡ ከተማው ፡ በቍስጥንጥንያ ፡ ተሆነ ፡ ወዲህ ፡ የቤት ፡ ሥራ ፡ ብልሀት ፡ ተሮም ፡ አቋረጠ ። በዚህ ፡ ዘመን ፡ የሮማውያን ፡ ወይም ፡ የቤተ ፡ ጣዖትና ፡ የጥንት ፡ የታላላቅ ፡ ቤቶች ፡ ዐምድ ፡ ተሰበሰቡ ።

፯ ፤ እነዚህን ፡ እጅግ ፡ በብልሀት ፡ የተሠሩትን ፡ ያማሩ ፡ ሕንፃዎች ፡ ጎቶችና ፡ ባንዳሎች ፡ ፈጽመው ፡ አጥፍተዋቸው ፡ ነበሩ ። ነገር ፡ ግን ፡ ቴዎዶሪክ ፡ የተባለ ፡ አንድ ፡ የዕውቀት ፡ ወዳጅ ፡ የነበረ ፡ ሰው ፡ ሊጠግናቸው ፡ ፈለገ ፡ (ፈተነ ፡ )እንዲያውም ፡ አያሎች ፡ አዲስ ፡ ቤቶችን ፡ ሠራ ። የዛሬው ፡ የቤት ፡ ሥራ ፡ ዐይነት ፡ በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ይሠራ ፡ ከነበረው ፡ ይመሳሰላል ። የሕንፃውንም ፡ መልክ ፡ የጎቶች ፡ ሥራ ፡ ይሉታል ።

፰ ፤ የቤት ፡ አሠራርን ፡ ብልሀት ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ አገር ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ብልሀት ፡ አግኝ ተውለታል ። በልዩ ፡ ልዩ ፡ ዘመን ፡ ሲነሣና ፡ ሲወድቅ ፡ ቈይቶአል ። ባሜሪካ ፡ የሆነ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የግሪኮችን ፡ የቤት ፡ አሠራር ፡ ዐቅድ ፡ ተከትለዋል ። ይኸም ፡ ጎቶች ፡ የሚሠሩት ፡ ትንንሽ ፡ ቤት ፡ የተሻለ ፡ ሆኖ ፡ አግኝተውታል ። ውበቱን ፡ ለመግለጥ ፡ ተብሎ ፡ እንደሚታይ ፡ አድርጎ ፡ መሥራት ፡ አያስፈልግም ።

፱ ፤ ስለ ፡ ግብርና ፡ ሥራ ፡ የመጀመርያው ፡ (ማስታወቂያ ፡) ማመልከቻ ፡ በሙሴ ፡ መጻሕፍት ፡ ይገኛል ፤ ቃየል ፡ ምድር ፡ አራሽ ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ ከነዚህ ፡ መጻሕፍት ፡ እንማራለን ። ኖኅም ፡ የተክል ፡ ሥራ ፡ ያውቅ ፡ እንደ ፡ ነበረ ፤ ወይም ፡ ይተክል ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ እርግጥ ፡ ነው ።

፲ ፤ ቺኖች ፤ ጃፓኖች ፤ ከለዳውያን ፤ ግብፃውያን ፤ ፈኒቂያውያን ፤ ጥንት ፡ ዘመን ፡ ዋና ፡ ሥራቸው ፡ ወይን ፡ መትከል ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ የታወቀ ፡ ነው ። ከርታጎችም ፡ የዚህን ፡ ሥራ ፡ እያራቀቁ ፡ በብልሀት ፡ ከፍ ፡ ወደ ፡ አለ ፡ ደረጃና ፡ ወደ ፡ ፍጻሜ ፡ አደረሱት ። የግሪክ ፡ የእርሻ ፡ መሣሪያዎች ፡ እጅግ ፤ ቀላሎች ፡ ሳሉ ፡ ጥቂቶች ፡ ናቸው ። ሮማውያን ፡ ብዙውን ፡ የእርሻ ፡ መሣሪያ ፡ ለጥቅማቸው ፡ ያደርጉታል ። በተለየም ፡ ማረሻውን ፡ ይወዱታል ።

፲፩ ፤ ለወጥ ፡ ቤት ፡ የሚሆን ፡ ቅጠላ ፡ ቅጠል ፡ ዘወትር ፡ እንዲገኝ ፡ የአታክልት ፡ ሥራ ፡ ከጥንት ፡ ጀምሮ ፡ እንደ ፡ ተጠበቀ ፡ ይኖራል ። ይህም ፡ ሕዝብ ፡ ወደ ፡ ሥልጣኔ ፡ ደረጃ ፡ በደረሰበት ፡ ሁሉ ፡ ይደረጋል ። ደግሞ ፡ በሠለጠኑት ፡ ሕዝብ ፡ እንደ ፡ ጌጥ ፡ እየተደረጉ ፡ በየመተላለፊያውና ፡ በየግንቡ ፡ ላይ ፡ የተተከሉ ፡ አታክልቶችና ፡ አበባዎች ፡ በሚያስፈልገው ፡ ስፍራ ፡ የሚደረጉት ፡ ሁሉ ፡ ለሰው ፡ የደስታ ፡ ስሜት ፡ እንዲሰጡ ፡ ተብሎ ፡ ነው ።

፲፪ ፤ የሲሚራሚስ ፡ የተንጠለጠለው ፡ አታክልትና ፡ መሬቱ ፡ በምሰሶ ፡ ከፍ ፡ ብሎ ፡ ተሠርቶ ፡ ተይዞ ፡ ውሃ ፡ በብልሀት ፡ አድርገው ፡ የሚያጠጡት ፡ እጅግ ፤ የሚያስደንቅ ፡ ነበር ።

፲፫ ፤ ግሪኮች ፡ በብልሀት ፡ ስለሚደረገው ፡ አታክልት ፡ እጅግ ፡ አድርጎ ፡ የሚያስደንቅ ፡ የላቸውም ። ስለ ፡ ሮማያውን ፡ የአታክልት ፡ ሥራ ፡ ልብ ፡ ታደርጉት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የፕሊንን ፡ መንደር ፡ ወይም ፡ መቀመጫ ፡ አሳስቤያችሁ ፡ ነበር ፡ እጅግ ፡ ደስ ፡ አያሰኝም ፡ እንጂ ፡ ሥራው ፡ በብልሀት ፡ የተሠራ ፡ ነው ።

፲፬ ፤ የደቡብን ፡ ኤውሮጳ ፤ አራዊት ፡ ሕዝብ ፡ ከተናኙበት ፡ ጊዜ ፡ ጀምሮ ፡ ቻርለማኝ ፡ አገሩን ፡ እስኪያድሰው ፡ ድረስ ፡ በብልሀት ፡ እየተጌጠ ፡ የሚሠራው ፡ የአታክልት ሥራ ፡ ጥበብ ፡ መሠራቱ ፡ ቀርቶ ፡ ነበር ።

፲፭ ፤ በሉዊስ ፡ ፲፬ኛ ፡ ጊዜ ፡ በፈረንሳይ ፡ አዲስ ፡ መልክ ፡ ገባ ። እንደዚሁ ፡ እንደ ፡ አዲሱ ፡ ሁኔታ ፡ የመተላለፊያውን ፡ መንገድ ፡ በብልሀት ፡ እየደለደሉ ፡ በቀጥታ ፡ ይሠሩታል ።

፲፮ ፤ ዳር ፡ ዳሩን ፡ ዛፍ ፡ ይተክሉበታል ። ከዚሁ ፡ አያሎቹን ፡ እየቈረጡ ፡ ፒራሚድ ፡ የሣር ፡ ክምር ፡ ሌላም ፡ የልዩ ፡ ልዩ ፡ የአውሬ ፡ መልክ ፡ እያስመሰሉ ፡ ያበቦችንም ፡ ስራፍ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ መልክ ፡ እያደረጉ ፡ ይሠሩታል ። የውሃ ፡ መፍሰሻውን ፡ የእንቍራሪት ፤ የአንሽላሊት ፤ የአንበሳ ፤ የአዞ ፡ መልክ ፡ እያስመሰሉ ፡ ይሠሩታል ።

፲፯ ፤ የዚህም ፡ የብልሀት ፡ ሥራ ፡ በሆላንድና ፡ በእንግላንድ ፤ በሌሎትም ፡ አገር (ገባ) ታወቀ ፤ በኋላ ፡ ግን ፡ ከጥንት ፡ ጀምረው ፡ ቻኖችና ፡ ጃፓኖች ፡ ይህን ፡ የአትክልት ፡ ጌጥ ፡ ሥራ ፡ ይሠሩትና ፡ እጅግ ፡ ያማሩትንም ፡ አበቦትና ፡ ቊጥቋጦችን ፡ ዛፎችንም ፡ እየሰበሰቡ ፡ ይተክሉ ፡ እንደ ፡ ነበሩ ፡ ታወቀ ።

፲፰ ፤ የተፈጥሮ ፡ ውበታቸውን ፡ ለማግኘት ፡ የሚችሉትን ፡ ያህል ፡ ተከታተሉ ። ይህንም ፡ እንግሊዞች ፡ በአገራቸው ፡ አደረጉት ። ዛሬውንም ፡ ቢሆን ፡ በብልሀት ከተደረገው ፡ ሥራ ፡ የበለጠ ፡ ደስታ ፡ አልሰጠም ።

## ጥ ያ ቄ ።

፩ ፤ ሰው ፡ ሲባል ፡ መጀመርያ ፡ ነገድ ፡ (ሕዝብ) የሆነው ፡ እንዴት ፡ ነው ፡ ?
ሥልጥንና ፡ እየገፉ ፡ ሲሄድ) ምን ፡ (ተባለ) ፡ ተደረገ ፡ ?

፪ ፤ የቤት ፡ መሥራት ፡ ዕውቀት ፡ እንዴት ፡ ነበር ፡ ?

፫ ፤ ስለ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ዐይነት ፡ የቤት ፡ አሠራርና ፡ መልክ ፡ ተናገር ።
የቤት ፡ አሠራር ፡ ብልሀት ፡ እያደር ፡ እንዴት ፡ ነበር ፡ ?

፬ ፤ ጥንት ፡ ስለ ፡ ቤት ፡ መሥራት ፡ ብልሀት ፡ የሚጠነቀቁ ፡ የትኞች ፡ ሕዝቦችናቸው ፡ ?
የፋርሶችና ፡ የግብፆች ፡ አሠራር ፡ እንዴት ፡ ነው ፡ ?

፭ ፤ ግሪኮች ፡ እንዴት ፡ ሆኑ ፡ ?
የቤት ፡ አሠራራቸው ፡ እንዴት ፡ ነው ፡
የሮማውያን ፡ ሕንፃ ፡ እንዴት ፡ ያለ ፡ ነው ፡ ?

፮ ፤ የጐቶችና ፡ የባንዳሎች ፡ እንዴት ፡ ያለ ፡ ነው ፡ ?
የቴዎዶሪኮችስ ፡ ?

የገጠሮች ፡ የቤት ፡ ሥራ ፡ ዕውቀት ፡ እንዴት ፡ ነው ፡ ?

፰ ፤ የአሜሪኮች ፡ የቤት ፡ ሥራ ፡ ዕውቀት ፡ እንዴት ፡ ነው ፡ ?

፱ ፤ በቅዱስ ፡ መጽሐፍ ፡ ስለ ፡ ግብርና ፡ ስለ ፡ እርሻ ፡ እንዴት ፡ ተባለ ፡ ?

፲ ፤ መሬትን ፡ ስለ ፡ ማረስ ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ መንግሥታት ፡ እንዴት ፡ ሆነ ፡ ?

፲፩ ፤ ስለ ፡ ተክል ፡ ዕውቀት ፡ እንዴት ፡ ሆነ ፡ ?
የጌጥ ፡ አተካከል ፡ ብልሀትስ ፡ ?

፲፪ ፤ የሴሚራሚስ ፡ አታክልት ፡ እንዴት ፡ ነበር ፡ ?

፲፫ ፡ የግሪኮች ፡ እንዴት ፡ ነው ፡ ? የሮማውያንስ ፡ ?

፲፬ ፤ አታክልት ፡ ከኤውሮጳ ፡ እንደምን ፡ ጠፋ ፡ ?
እንደ ፡ ገና ፡ ያደሰው ፡ ማነው ፡ ?

፲፭ ፤ በሉዊስ ፡ ፲፬ኛ ፡ እንዴት ፡ ያለ ፡ ብልሀት ፡ ተገኘ ፡ ?
አታክልት ፡ በቺንና ፡ በጃፓን ፡ በእንግሊዝ ፡ አገር ፡ እንዴት ፡ ነው ፡ ?

---

## ምዕራፍ ፻፲፫ ፡ ዋና ፡ የሚታይ ።

### ንግድ ።

፩ ፤ መጀመርያ ፡ ሰዎች ፡ ያደርጉት ፡ የነበረው ፡ እርስ ፡ በርሳቸው ፡ በንግድ ፡ መገናኘታቸው ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ በኦሪት ፡ ዘፍጥረት ፡ በ፴፯ ፡ በቍጥር ፡ ፳፭ ፡ ይገኛል ። ይኸውም ፡ ዮሴፍን ፡ ወንድሞቹ ፡ ሸጡና ፡ ቅመም ፡ ከርቤም ፡ ይዘው ፡ ለሚዞሩ ለእስማኤላውያን ፡ በመሸጣቸው ፡ ይታወቃል ። ባም ፡ ተገልአድ ፡ ከርቤ ፡ ከዐረብ ፡ አገር ፡ ይገኝ ፡ ስለ ፡ ነበር ፡ በከነዓን ፡ አድርገው ፡ በጣም ፡ ወደ ፡ ሠለጠነው ፡ መንግሥት ፡ ወደ ፡ ምስር ፡ ይሄዱ ፡ ነበር ።

፪ ፤ መቸውንም ፡ የመኻል ፡ ግብፅ ፡ ሁኔታ ፡ የንግድ ፡ ዕቃ ፡ መቆሚያ ፡ ነበር ። በጭነት ፡ እየሆነ ፡ የእስያና ፡ የአፍሪካ ፡ ሸቀጥ ፡ ወደዚህ ፡ ይመጣ ፡ ነበር ። ማለት ፡ ሀብትን ፡ የሚያመጣ ፡ (የሚያስገኝ ፡) ንግድ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ መቼውንም ፡ የተከበረ ፡ ነው ። ግብፃውያን ፡ የባሕርን ፡ አምልኮ ፡ ከብዙ ፡ ዘመን ፡ ጀምሮ ፡ ቸለል ፡ ስለ አሉ ፡ ስለ ፡ ባሕር ፡ ንግድ ፡ የምናውቅላቸው ፡ ነገር ፡ የለም ።

፫ ፤ ጢሮስና ፡ ሲዶን ፡ የተባሉት ፡ የፊኒቅያ ፡ ከተሞች ፡ የታወቁት ፡ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ነው ። አገሮቻቸው ፡ የሚሰጡት ፡ ሀብት ፡ የላቸውም ። ጥቂትም ፡ ቢገኝ ፡ በእጅ ፡ ሥራ ፡ ነው ። ንግዳቸውን ፡ ከጠረፍ ፡ ወደ ፡ ጠረፍ ፡ እያዘዋወሩ ፡ ያከበሩዋቸው ፡ በእጅ ፡ ሥራ ፡ ነው ።

፬ ፤ ተክርስቶስ ፡ ልደት ፡ በፊት ፡ ፩ሺ ፡ ፩፻ ፡ ዓመት ፡ በዳዊት ፡ ዘመን ፡ ፊኒቅያውያን ፡ ንግዳቸውን ፡ ሁልጊዜ ፡ በውነተኛ ፡ መንፈስ ፡ እያሰፉ ፡ ስለ ፡ ሄዱ ፡ ብዙ ፡ ወርቅ ፡ ከእስጳንያ ፡ አገኙ ። በንግዳቸውም ፡ ምክያት ፡ መኖሪያቸውን ፡ በዚያው ፡ አደረጉ ።

፭ ፤ ሰሎሞንም ፡ የንግድን ፡ ጥቅም ፡ በተመለከተ ፡ ጊዜ ፡ መርከቦች ፡ አሠራና ፡ ወደ ፡ አፌር ፡ እየሰደደ ፡ ወርቅና ፡ ብር ፤ የዝሆን ፡ ጥርስ ፡ ወፎችና ፡ ሌላም ፡ ነገር ፡ ያስመጣ ፡ ጀመር ። ተምስሮችም ፡ ጋር ፡ ታላቅ ፡ ንግድ ፡ ነበረው ። ከዚያ ፡ ፈረሶችና ፡ የአማረ ፡ የተልባ ፡ እግር ፡ ያገኝ ፡ ነበር ።

፮ ፤ ተክርስቶስ ፡ ልደት ፡ በፊት ፡ ፰፻፷፱ ፡ ዓመት ፡ የካርታጎ ፡ ከተማ ፡ ተሠራና ፡ ንግዱም ፡ በሠለጠነው ፡ መላ ፡ ዓለም ፡ ታወቀ ። ተክርስቶስ ፡ ልደት ፡ በፊት ፡ ፯፻ ፡ ዓመት ፡ ሲሆን ፡ ቆሮንቶስ ፡ በባሕር ፡ ንግድ ፡ ረገድ ፡ ኀይሉ ፡ በጣም ፡ የተለየ ፡ ሆነ ። መርከብም ፡ በመሥራት ፡ እየተሻሻለ ፡ ሄደ ።

፯ ፤ ተክርስቶስ ፡ ልደት ፡ በፊት ፡ ፭፻፹፰ ፡ ጢሮስ ፡ ስመ ፡ ጥሩ ፡ ሆነች ፤ ስለ ፡ ንግዱዋና ፡ እታይ ፡ እታይ ፡ ስለማትዋ ፡ በሕዝቅኤል ፡ ፳፮ኛና ፡ ፳፰ ፡ ምዕራፍ ፡ ተመልክተናል ። ነገር ፡ ግን ፡ የጢሮስ ፡ ሕዝብ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ በቀል ፡ በራሳቸው ፡ ላይ ፡ አምጥተዋልና ፤ መጀመርያ ፡ ናቡከደነ ፡ ፆር ፡ ገዛቸው ። ተዚያም ፡ ተክርስቶስ ፡ ልደት ፡ በፊት ፡ ፫፻፴፪ ፡ ዓመት ፡ እስክንድር ፡ ሰጥ ፡ አድርጎ ፡ ገዛቸው ።

፰ ፤ ፊኒቃውያን ፡ ጢሮስ ፡ ከጠፉች ፡ በኋላ ፡ ከተማዋን ፡ ሮማውያን ፡ እስኪያጠፏዋት ፡ ተክርስቶስ ፡ ልደት ፡ በፊት ፡ ፻፵፮ ፡ ድረስ ፡ በካርታጎ ፡ በኩል ፡ እያደረጉ ፡ ንግዳቸውን ፡ ያሰፉ ፡ ነበር ። አንድ ፡ ጊዜ ፡ የግሪኮች ፡ መንግሥታት ፡ በባሕር ፡ ረገድ ፡ እጅግ ፡ አድ ርገው ፡ በርትተው ፡ ደምቀው ፡ ይታዩ ፡ ነበር ። አቴንና ፡ እስፓርታም ፡ በተራ ቸው ፡ ስማቸው ፡ በሁሉ ፡ ዘንድ ፡ ታወቀላቸውና ፡ መጥፊያቸው ፡ እስኪደርስ ፡ እንዲሁ ፡ ቈዩ ።

፱ ፤ እስክንድር ፡ በንግድ ፡ ጕዳይ ፡ እጅግ ፡ አሰበና ፡ የእስክንድርያንና ፡ የቤርኒስን ፡ ከተሞች ፡ ሠራ ። ከነዚህ ፡ ስፍሮች ፡ አያይዞ ፡ በሜዲቴራኒያን ፡ ባሕር ፡ እያደ ረገ ፡ ወደ ፡ ምዕራብ ፡ ንግዱን ፡ አሰፋ ። ከወዲህም ፡ በቀይ ፡ ባሕር ፡ እያደረገ ፡ ሀብታም ፡ ከሆኑ ፡ ከምሥራቅ ፡ አገሮችና ፡ ከመኻከል ፡ እስያ ፡ ጋር ፡ በሱዝ ፡ በር ፡ እያስተላለፈ ፡ ንግዱን ፡ ያሰፋ ፡ ነበር ። ብዙ ፡ የንግድ ፡ መርከቦች ፡ ስለ ፡ ነበሩት ፡ ገቢ ፡ ገንዘብ ፡ ያለመጠን ፡ ያገኝ ፡ ነበር ።

፲ ፤ ሮማውያን ፡ ጭራሽ ፡ የንግድን ፡ ጥቅም ፡ አያውቁም ፡ ነበር ። የንግድን ፡ ሥራ ፡ ጭራሽ ፡ ለማጥፋት ፡ እንዳሰቡት ፡ የግሪክ ፡ ዋና ፡ የንግድ ፡ ከተማ ፡ የነበረችውን ፡ ቆሮንቶስን ፡ አጠፏዋት ። ወዲያው ፡ በዙሪያው ፡ ላሉ ፡ አገሮች ፡ የተሰማቸው ፡ ታላቅ ፡ የንግድ ፡ ጥፋት ፡ ተከተለ ። ቆሮንቶስና ፡ ካርታጎን ፡ ባንድ ፡ ዓመት ፡ ሊያ ድሳቸው ፡ የፈለገ ፡ ጁሊውስ ፡ ቄሣር ፡ የሚነግሥበት ፡ ጊዜ ፡ እስኪደርስ ፡ ድረስ ፡ እንዲሁ ፡ ሆነ ።

፲፩ ፤ ሮማውያን ፡ በሜዲቴራኒያን ፡ ባሕር ፡ ዙሪያ ፡ ባሉት ፡ አገሮች ፡ ላይ ፡ ጌቶች ፡ ስለ ፡ ሆኑ ፡ ለራሳቸው ፡ ሲሉ ፡ ንግድን ፡ ፈቀዱላቸው ። ስለዚህ ፡ በዚያ ፡ ዙሪያ ፡ ካለው ፡ አገር ፡ ሁሉ ፡ ለሚያስፈልጋቸውና ፡ ለአዱኛቸው ፡ የሚበቃ ፡ ገቢ ፡ ገንዘብ ፡ በዛላቸው ። ስለ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ጕዳይ ፡ የተመረጡትን ፡ ዕቃዎች ፡ መልስ ፡ ገንዘብ ፡ አደረጉ ። የዚህም ፡ መለዋወጥ ፡ ንግድ ፡ ይባላል ። በውነትም ፡ ሮማውያን ፡ የን ግድ ፡ ሰዎች ፡ አልነበሩም ። ንግድ ፡ የሚባለው ፡ በፊታቸው ፡ የተናቀ ፡ ሆነና ፡ ምኞታቸው ፡ አገር ፡ መግዛት ፡ ሆኖ ፡ ሀብትን ፤ ብልጽግናን ፡ በሰይፋቸው ፡ ብቻ ፡ ለማግኘት ፡ ወደዱ ።

፲፪ ፤ ዋናው ፡ የመንግሥት ፡ መኖሪያ ፡ ወደ ፡ ቍስጥንጥንያ ፡ ከሆነ ፡ ወዲህ ፡ ቴዎዶ ሪክ ፡ የተባለ ፡ የኢጣሊያ ፡ ንጉሥ ፡ ሆነ ። ሰላምና ፡ ጥበብ ፡ በመላበት ፡ በርሱ ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ፡ ምንም ፡ በሁለመናው ፡ ባይሳካለት ፡ ንግድ ፡ እንደ ፡ ገና ፡ እየገ ነነ ፡ ሄደ ። ሐር ፡ በምሥራቅ ፡ አገር ፡ ዋና ፡ የንግድ ፡ ዕቃ ፡ ሆነ ። ፋርሶችም ፡ ከህ ንድ ፡ የሚአመጡአቸው ፡ መርከቦች ፡ የሚያርፉት ፡ በጠረፋቸው ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ በን ግዳቸው ፡ ሀብታሞች ፡ ሆኑ ።

፲፫ ፤ ተክርስቶስ ፡ ልደት ፡ በኋላ ፡ ፲፻፹፱ ፡ ዓ. ም. ቤኒስ ፡ ንግዷን ፡ ወደ ፡ ምሥራቅ ፡ እያሰ ፋች ፡ ሄደች ። የጣሊያኖች ፡ አውራጃዎችም ፡ ንግዳቸውን ፡ ከልዩ ፡ ልዩ ፡ አገሮች ፡ ጋር ፡ ይነግዱ ፡ ጀመር ። በሺ ፡ ፫፻ ፡ ፒሳና ፡ ጀኖዋ ፡ የንግድ ፡ ከተሞች ፡ በመሆ ናቸው ፡ የተለዩ ፡ ሆኑ ።

፲፬ ፡ በሺ፡፷፮ ፡ ዊልየም ፡ አሸናፊው ፡ የተባለ ፡ በእንግሊዝ ፡ ዙፋን ፡ ሲቀመጥ ፡ በዚህ ፡ አገር ፡ ንግድ ፡ ተጀመረ ፡ ብለን ፡ እንቈጥራለን ። ኖርማንዲና ፡ እንግላንድ ፡ በዚያን ፡ ጊዜ ፡ መተዋወቅ ፡ ጀመሩ ።

፲፭ ፡ ወደፊት ፡ የሚመጣውን ፡ ንግድ ፡ ያነሣሡና ፡ ያበረታቱ፡የመስቀል ፡ ጦር ፡ ጭፍሮች ፡ እንደ፡ነበሩ ፡ ተረድተነዋል ። የመስቀል ፡ ጦር ፡ ጭፍሮች ፡ በምሥራቅ ፡ የሚያገኙትን ፡ ደስታ ፡ በአገራቸው ፡ አያገኙትምና ፡ የውጭ ፡ አገርን ፡ ውበትና ፡ ምቾት ፡ ለማግኘት ፡ ተጣጣሩ ። ስለዚህ ፡ ንግድ ፡ በፍጥነት ፡ በገዛ ፡ ራስዋ ፡ እየሰፋች ፡ ለመሄድ ፡ ጀመረች ።

፲፮ ፡ ነሐስና ፡ መዳብ ፡ ጥሩ ፡ ብረትም ፡ መገኘቱ ፡ ለንግድ ፡ አዲስ ፡ (ክንፍ ፡) መንገድ ፡ ሰጣት ። በሺ፡፪፻ ፡ በመርከብ ፡ መተላለፍ ፡ ተቻለ ። በንጉሥ ፡ ጆን ፡ ዘመን ፡ በሺ፡፪፻፲፮፡ነጋዴዎች ፡ ስለ፡በዙ ፡ እንግላንድ ፡ ሀብታም ፡ ሆነ ። ሕዝቡም ፡ በጣም ፡ ሀብታሞች ፡ ሆኑ ።

፲፯ ፡ በሺ፡፫፻፵፩ ፡ የጀርመኖች ፡ መንደሮች ፡ ንግድ ፡ ጀመሩ ። እርስ ፡ በርሳቸው ፡ ለመደጋገፍ ፡ ብለው ፡ አንድ ፡ ማኅበር ፡ አቆሙ ። ሐንስ ፡ የተባሉት ፡ ከተሞች ፡ በጣም ፡ ሀብት ፡ አገኙና ፡ እጅግ ፡ ኀይለኞች ፡ ሆኑ ፤ ኤድዋርድ ፡ አንደኛ ፡ የተባለ ፡ እንግሊዝ ፡ በንግድ ፡ ትልቅ ፡ ኀይል ፡ እንዲያገኙ ፡ ፈቀደላቸው ። ስለ፡ሆነ ፡ በኤድዋርድ ፡ ፫ኛ ፡ ንግድ ፡ አቋረጠ ።

፲፰ ፡ በንግሥት ፡ ኤልሳቤጥ ፡ ዘመን ፡ ንግዳቸውን ፡ ሌላ ፡ መሰናክል ፡ አገኘው ። ከዚህም ፡ ሁሉ ፡ ጋር ፡ የሚያስፈሩ ፡ ሆኑና ፡ የብዙ ፡ አገሮች ፡ መንግሥታት ፡ባንድነት ፡ ሆነው ፡ በጠላትነት ፡ ተነሡባቸው ፡ ኀይላቸውም ፡ ደከመና ፡ በመጨረሻው ፡ በሺ ፡ ፭፻፷፱ ፡ ጭራሽ ፡ ወደቁ ።

፲፱ ፡ በ፲፬፻፶፩ ፡ ፍሎሬንስ ፡ የምትታይ ፡ ሆነች ። ንግዱዋም ፡ ሰፋ ። ፋብሪካዋም ፡ እጅግ ፡ ያማረና ፡ ዋጋ ፡ ያለው ፡ ሆነ ። ነጋዶችም ፡ ብዙ ፡ ገንዘብ ፡ ሰባሰቡና ፡ የመላው ፡ ኤውሮጳ ፡ ባንክ ፡ ሆኑ ፤ እንዲህም ፡ ሆኖ ፡ ብዙ ፡ ዘመን ፡ ቈየ ።

፳ ፡ እንዲሁም ፡ በኤውሮጳ ፡ ዋና ፡ የእጅ ፡ ሥራ ፡ የሚታይበት፡ፍላንድር ፡ ነበር ። ባለፈው ፡ ፱፻፳ ፤ ብንመለከት ፡ የፍሌሚሽ ፡ ንግድ ፡ ጥቅም ፡ ያለው፡እንደ፡ነበረ ፡ እናያለን ። በሺ ፡ ፭፻፵፫ ፡ በተልባ ፡ እግር ፡ ሥራቸው ፡ ስመ ፡ ጥሩዎች ፡ ነበሩ ። የፖራማ ፡ ዱክ ፡ እስኪያጠፋቸው ፡ እስከ ፡ ሺ ፡ ፮፻፹፩ ፡ ድረስ ፡ በእጅ ፡ ሥራ ፡ በርትተውና ፡ ጠንክረው ፡ ነበር ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ያገሩ ፡ ጥቅም ፡ አቋረጠ ፤ የጅ ፡ ሥራም ፡ ወደሌሎች ፡ አገሮች ፡ ተበተነ ።

፳፩ ፤ ከዚህ ፡ ወዲያ ፡ በጭንነት ፡ እየሆነ ፡ ንግዱ ፡ ወደ ፡ ህንድ ፡ ዞረ ። ነገር ፡ ግን ፡ በሺ ፡ ፬፻ ፤ መንገደኞች ፡ መልካም ፡ ተስፋ ፡ የተባለውን ፡ አገር ፡ አገኙና ፡ የሀብትና ፡ የአዱኛ ፡ መንገድ ፡ ተከፈተ ። ሺ ፡ ፬፻ ፡ ፖርቱጊሶች ፡ ወደ ፡ አፍሪካ ፡ እየዞሩ ፡ መቀመጥ ፡ ጀመሩ ። ወዲያው ፡ ቶሎ ፡ ብሎ ፡ እስከ ፡ ሺ ፡ ፬፻፹ ፡ የፖርቱጋልን ፡ መንግሥት ፡ የእስጳንያ ፡ ንጉሥ ፡ በያዘው ፡ ጊዜ ፡ የንግድ ፡ መኻከለኛ ፡ ስፍራ ፡ ሆነ ።

፳፪ ፤ ከሺ ፪፻፲፮ ፡ ከጆን ፡ መንገሥ ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ሺ ፫፻፲፯ ፡ ድረስ ፡ ንግድ ፡ በእንግላንድ ፡ በጣም ፡ እየገነነ ፡ ሄደ ። ነገር ፡ ግን ፡ በእንግሊዝና ፡ በፍሊሚሽ ፡ ጠብ ፡ ጊዜ ፡ የንግድ ፡ ቤቶች ፡ ሁሉ ፡ አቆሙ ። በሺ ፫፻፴፩ ፡ በ፫ኛ ፡ ኤድዋርድ ፡ ዘመን ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ተንቀሳቀሱ ። እርሱም ፡ የጠጕርን ፡ ልብስ ፡ ብልሀት ፡ ያመጣ ፡ ነው ።

፳፫ ፤ በ፰ኛ ፡ ሄንሪ ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ መታደስ ፡ ለንግድ ፡ ዋና ፡ ጠቀሜታ ፡ ሆኖ ፡ ነበር ። በ፮ኛ ፡ ኤድዋርድ ፡ ዘመን ፡ ንግድ ፡ ወደ ፡ ረሺያ ፡ ገባ ። ንግድን ፡ በጣም ፡ የምታበረታ ፡ ንግሥት ፡ ኤልሳቤጥ ፡ ነበረች ። አያሎች ፡ ኩባንዮች ፡ አደ ረገችና ፡ አንዱን ፡ በረሺያ ፤ ሌላውንም ፡ በቱርክና ፡ በሊቫንት ፡ አቆመች ። በሺ ፮፻ ፡ በርስዋ ፡ መንግሥት ፡ ጊዜ ፡ የተጀመረው ፡ የምሥራቅ ፡ ህንድ ፡ ኩባንያ ፡ የንግድ ፡ ፈቃድ ፡ መስከረም ፡ ፩ ፡ ቀን ፡ ሺ ፰፻፶፰ ፡ ተፈጸመ ።

፳፬ ፤ በአሜሪካ ፡ ነጻነት ፡ ከታወጀ ፡ በኋላ ፡ በዚያ ፡ አገር ፡ የንግድ ፡ ቤቶች ፡ በጣም ፡ ከፍ ፡ እያሉ ፡ ሄዱ ። መርከቦቻቸው ፡ ወደ ፡ሩቅ ፡ ለመድረስ ፡ ባሕርን ፡ ከፍለው ፡ (ሠንጥቀው) ፤ አልፈው ፡ በየአገሩ ፡ የሚገኘውን ፡ ሀብት ፡ ይዘው ፡ ወደ ፡ አገራቸው ፡ ተመለሱ ። የንግዳቸው ፡ መከናወን ፡ እስከ ፡ አሁን ፡ በማይናወጥ ፡ መሠረት ፡ ላይ ፡ ቆሞአል ።

## ጥያቄ ።

፩ ፤ ጥንት ፡ ስለ ፡ ንግድ ፤ የተባለው ፡ ምንድነው ፡ ?
፪ ፤ ስለ ፡ ግብፅ ፡ ምን ፡ ይባላል ፡ ?
　　ንግዱ ፡ ምንድነው ፡ ?
፫ ፤ ስለ ፡ ጢሮስና ፡ ሲዶን ፡ ምን ፡ ይባላል ፡ ?
፬ ፤ ስለ ፡ ፊኒቂያ ፡ ምን ፡ ይነገራል ፡ ? ካዲዝ ፡ ምንድነው ፡ ?
፭ ፤ ሰሎሞን ፡ ንግድን ፡ እንዴምን ፡ አበረታታ ፡ ?
፮ ፤ ካርታጎ ፡ እንዴምን ፡ ሆነ ፡ ? ቆሮንቶስስ ፡ ?
፯ ፤ ጢሮስ ፡ እንዴምን ፡ ሆነ ፡ ?
፰ ፤ ፊኒቂያኖች ፡ ምን ፡ ያደርጉ ፡ ነበር ፡ ? አቴኖችና ፡ እስፓርቶችስ ፡ ?
፱ ፤ እስክንድር ፡ ስለ ፡ ንግድ ምን ፡ አደረገ ፡ ?
፲ ፤ ንግድ ፡ እንዴምን ቢሆን ፡ ተበላሸ ፡ ?
፲፩ ፤ ሮሞች ፤ ስለ ፡ ንግድ ፡ ምን ፡ አደረጉ ፡ ?
፲፪ ፤ በቴዎደሪክ ፡ ዘመን ፡ ንግድ ፡ እንዴምን ፡ ሆነ ፡ ? በምሥራቅ ፡ በፋርስ ፡ ?
፲፫ ፤ በቬኒስ ፡ ንግድ ፡ እንዴምን ፡ ሆነ ፡ ? ፒሳ ? ጀኔበ ፡ ?
፲፬ ፤ በእንግላንድ ፡ የንግድ ፡ መንቀሳቀስ ፡ እንዴት ፡ ሆነ ፡ ?
፲፭ ፤ ስለ ፡ መስቀል ፡ ጦርነት ፡ እንዴት ፡ ሆነ ፡ ?
፲፮ ፤ ማግኔት ፡ የሚስብ ፡ ብረት ፡ በመገኘቱ ፡ ምን ፡ ሆነ ፡ ?

፳፯ ፤ የሁንስ ፡ ከተሞች ፡ እንዴት ፡ ሆኑ ፡ ?

፳፰ ፤ ፍሎሬንስ ፡ እንደምን ፡ ሆነ ፡ ?

፴ ፤ የፍላንደርስ ፡ ንግድ ፡ እንዴት ፡ ሆነ ፡ ? ምን ፡ አጠፋው ፡ ?

፴፩ ፤ በህንድ ፡ በኩል ፡ ንግድ ፡ እንዴት ፡ ሆነ ፡ ? በፖርቱጋልሳ ፡ ?

፴፪ ፤ ንግድ ፡ በእንግላንድ ፡ እንዴት ፡ ሆነ ፡ ?

፴፫ ፤ ንግሥቲቱ ፡ ለንግድ ፡ አንዴት ፡ አድርጋ ፡ ታበረታ ፡ ነበር ፡ ?

፴፬ ፤ ንግድ ፡ በአሜሪካ ፡ እንዴት ፡ ሆነ ፡ ?

---